«አዎን በቁጥር ሰባት ሕንጻ ውስጥ ። »

ጐርቬር ነጻ መሊቀቁን ሲያረጋግጥ ከአነስተኛው ምሽግ ወጥቶ ወደ ሀል ሠፈር አቅጣጫ ያመራ ጀመር ። ትንሽ ከተራመደ በኋላ ግን ዞር ብሎ ወደ ጐን ቫልገ ተመለከተና ፤ «ይህ ነገር አላማረኝም..... ደስ አላለኝም..... ብትገድለኝ ይሻለኛል» አለው ።

«ሂድ..... ነጻ ለቅቄሃለሁ ብዬሃለሁ» አሰው ጐን ቫልገ ።

ጐርቬር ዓይኑን ወደ መንገዱ መልሶ እየራቀ ሔደ ። ከጐን ቫልገ ዓይን ሲሰወር ጐን ቫልገ ጐርቬርን ገደለው እንዲባል መሣርያውን ወደ ሰማይ ተኮሰው ። ከዚያ በኋላ ወደ ዋናው ምሽግ ተመልሶ ፤ «ጨርሼው መጣሁ!» አላቸው ለአመጸኞቹ ።

— 4 —

ወጊያው እንደገና ተፋፋመ ። መድፍ ያጓራል ። እግረኛው ጦር ፣ ብሔራዊው ዘበኛ ፣ የማዘጋጃ ቤቱ ዘበኞችና እንዲሁም ምሽጉን ለማፍረስ መጥረቢያ ይዘው የወጡት ሠራተኞች ታምቡር እየመቱ ፣ መለከት እየነፉ ፣ ሳንጃ እየወደሩ ወደ ምሽጉ ሲጮሁ ይታያሉ ።

አመጸኞቹ በበኩላቸው ጠመንጃቸውን ያንጣጣሉ ። ወታደሮቹ እን ደማዕበል መጥተው ሲያጠቁ ፣ አመጸኞቹ ተኩስ ከፍተው ሲከላከሉ ፣ ሌላ የወታደር ማዕበል መጥቶ ሲያጠቃ ፣ አሁንም አመጸኞቹ ባላቸው ኃይል ሲከላከሉ ረጅም ጊዜ አለፈ ። አጥቂዎቹና ተከላካዮቹ በቁጥር ፈጽሞ አይመጣጠኑም ። ምናልባት በአጥቂው ወገን ላሉት ስድስ ሰዎች በተከላ ካዩ ወገን አንድ ሰው ቢኖር ነው ። አመጸኞቹን ስጊዜውም ቢሆን ከእልቂት የከለላቸው ምሽጋቸው ነበር ።

ከምሽጉ ውጭ ያለው መንገድ ሬሳ በሬሳ ሆነ ። ከምሽጉ ውስጥ ደሞ የጥይት ቀለሀ መሬት ላይ እንደበረዶ ተነሰንሷል ።

ኤንጐልራ ጠላት በማያየው ጥግ ሆኖ ምስት ወታደሮችን ጣለ ። ማሪዩ ግን ለጥቃት በተጋለጠ ሁኔታ ሲዋጋ ነበር ።

አጥቂዎቹ ምሽጉን ለመያዝ የተደጋገመ ሙከራ ቢያደርጉም አልተሳ ካላቸውም ። አመጸኞቹ ለሀያ አራት ሰዓታት ምግብ ባይቀምሱም ፣ ግማሾቹ ቀደም ብለው የቆሰሉ ቢሆኑም ፣ በቂ ጥይት ባይኖራቸውም ያንን ሁሉ ጦር ሠራዊት ግትረው ያዙት ። በእውነተኛ ቆራጥነትና ጀግንነት ተጋደሉ ። ከሩቅና ከቅርብ ፣ ከፎቁና ከጣራው ፣ ከምሽጉም ላይ በመሆን ባላቸው

@OLDBOOKSPDF

መሣሪያ ሁሉ ፤ ማለት በሰላት ፥ በሽጉጥ ፥ በጠመንጃ ፥ ሲያስፈልግም በጡጫ ታግሉ ።

የኮረንት ሕንጻ በወረደበት የጥይት ናዳ ምክንያት ወንፊት ሆነ ። መስኮቶቹ ረገፉ ። ከአመጸኞቹም ብዙዎቹ ወደቁ ። ቦሱዊ ወደቀ ። ሬዩ ወደቀ ። ኩርፌራ ወደቀ ። ኮምበፌር ወደቀ ። ማሪዩ ክፉኛ ቆሰለ ። ኤን ገርልራ ብቻ እስካሁን ሳይነካ ቆየ ።

ወታደሮቹ የምሽጉን መሐል ደጋግመው ሲመቱት በይበልጥ እየተ ደረማመስ ሔዱ ። በሕይወት የነበሩትም አመጸኞች ወደጎሳቸው ማፈግ ፈግ ጀመሩ ። ኤንገርልራና ማሪዩ ብቻ ከምሽጉ ግራና ቀኝ ጥግ ሆነው መከላከላቸውን ቀጠሉ ።

ያፈገፈጉት አመጸኞች የኮረንትን ቡና ቤት በር ከፍተው ገቡ ። በመ ጨረሻም ኤንገርልራ ራሱ አፈግፍጎ ከዚያ ገብቶ በሩን ሲዘጋው አንዱ ወታደር ተከታትሎት ሔዶ በሩን አላስዘጋ አለው ። ኤንገርልራም በሩን በጎይል ስቦ ሲዘጋው የወታደሩ እጅ ገባ ብሎ ኖሮ በዚያው ተቀርጥፎ ወደቀ ።

ማሪዩ ብቻውን እውጭ ቀርቶ ሲከላከል ሳለ ከአንገቱ ሥር ያለው አጥንት በጥይት ተመታ ። ዝሎ ሲወድቅ የሰው እጅ እንዳረፈበት ተሰ ማው ። «ማረኩኝ.....! ሊጨርሱኝ ነው.....!» ሲል አሰበ ።

ወታደሮቹ ምሽጉን ሰብረው ከገቡ በኋላ ወዲ ቡና ቤቱ በር ሔደው በሰደፍ ይደበድቡት ጀመር ። አሱንም ሰብረው ሲገቡ ከዚያ ውስጥ የማበ ፍና የጋቸሮሽ አስከሬን እንጂ በሕይወት ያለ ሰው የለም ። አመጸኞቹ እስከመጨረሻው ለመጋደል ቆርጠው ደረጃውን ወጥተው ድንጋይና ጠር ሙስ ይዘው በአንደኛው ፎቅ ላይ ሆነው ይጠባበቃሉ ። አመጸኞቹ አላይ ከወጡ በኋላ መውጫውን ደረጃ ለማፈራረስ ሙከራ አደረጉ ፤ ከጥቅም ውጭ ሊያደርጉት ግን አልቻሉም ።

ወታደሮቹ በተደረማመሰው ደረጃ ወዲ አንደኛው ፎቅ መውጣት ጀመሩ ። አመጸኞቹም ቢያዙት ድንጋይና ጠርሙስ ይወግሯቸው ጀመር ። ወታደሮቹ በበኩላቸው ያገኙትን አመጸኛ ሁሉ ረፈረፉት በቁጣ..... በን ዴት ።

ወታደሮቹ ከአንደኛው ፎቅ ሲደርሱ በሕይወቱ ያለ ከአለ አንድ ሰው በስተቀር አላገኙም ። የተረፈረፉት ተረፍርፈው የተቀሩት ወዲ ሁለተኛው ፎቅ ሸሽተው ወጥተው ነበር ። በአንደኛው ፎቅ የቀረው ኤንገርልራ ብቻ ነበር ። እስካሁን ድረስ ጥይትም ሆነ ስለት አልነካ ውም ። በእጁ አንድ ጥይት እንኳ አልቀረውም ። ጠመንጃውም ሲጋ ደልበት ተሰብሮበት ጉማጁ ብቻ በእጁ ቀርቷል ።

@OLDBOOKSPDF

«መሪው እሱ ነው!» አያሉ ይጨጫሡ ገቡ ወታደሮቹ ፤ «መድፍ ተኳሻችንን የገደለው እሱ ነው..... ባለበት መግደል አለበት!»

«ግደሉኝ!» አላቸው ኤንጐልራ የጠመንጃውን ጉማጅ ወዲያ ወረወረና ። የኩራት እንጂ የፍርሃት ስሜት አላሳየም ።

አስራ ሁለት ወታደሮች ጠመንጃቸውን ደገኑበት ።

«አነጣጥሩበት»! አለ አንድ የአምሳ አለቃ ።

«እስቲ ቆይ!» አለ ሌላ መኰንን ። ቀጠል አድርጎም ፤ «ዓይንህ በጨርቅ እንዲሸፈንልህ ትፈልጋለህ?» ሲል ጠየቀው ኤንጐልራን ።

«አልፈልግም!» አለው ኤንጐልራ ።
«መድፍ ተኳሻችንን የገደልከው አንተ ነህ?»
«አዎን ነኝ ።»

መኰንኑና ኤንጐልራ ይህንን ቃል ሲለዋወጡ ሳሉ ግራንቴር ከነበረበት ዓለም ነቃ ። ያ ሁሉ መድፍ ሲተኮስ ፥ ያ ሁሉ ጠመንጃ ሲንጣጣ በስካሩ ምክንያት ለሀያ አራት ሰዓት ሙሉ በድን ሆኖ ስለነበረ ምንም አልሰማም ። አሁን ግን ስካሩ አልፎለት ዓይኑን ገልጦ ዙርያውን ቢመለከት ሬሳ በሬሳ ተነባብሮ ታየው ። እሱ በስካርና በእንቅልፍ ዓለም ቦነበረበት ወቅት ምን እንደደረሰ ተገንዝቦ «ዕድሜ ለሬፑብሊኩ! እኔም ከአመጸኞቹ አንዱ ነኝ!» ሲል ጮኸ ። ወታደሮቹም ዓይናቸውን ወደ እሱ አዙረው ተመለከቱት ።

«ዕድሜ ለሬፑብሊኩ!» አሰ በድጋሚ ፥ ከነበረበት ተነስቶ ቆሞ ። ወደ ኤንጐልራም ሔድ ብሎ በአጠገቡ ቆመና ፤ «በአንድ ሳይ ግደሉን!» አለ ።

ወታደሮቹ ጠመንጃቸውን አንጐዳጐዱባቸው ። ኤንጐልራ በስምንት ጥይት ተደበደበ ። ይሁን እንጂ ጥይቶቹ ከግድግዳው ጋር ስፍትው የያዙት ይመስል ራሱን ዘንበል ከማድረግ በስተቀር ወዲያውኑ አልወደቀም ። ግራንቴር ግን በኤንጐልራ እግር ሥር ተዘረረ ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወታደሮቹ በላይኛው ፎቅ ያሉትን አመጸኞች ለማደን ደረጃውን እየተረማመዱ ወጡ ። ቦዚያ ያገኟቸውን እየገደሉ በመስኮት ይወረውሯቸው ጀመር ። እስከነነፍሳቸው በመስኮት የተወረወሩ ቁስለኞችም አልታጡም ። በሕንጻው ጣራ ላይ ደሞ አንድ ወታደርና ኦንድ አመጸኛ ግብግብ ተጋጠሙ ። እነ ታግሉ ወርደው ሁለቱም መሬት ላይ ተፈጠፈጡ ።

በሕንጻው ውስጥና በጣራው ላይ የነበሩት አመጸኞች ተገድለው ሲያልቁ ተኩሱ ፥ ትግሉ ፥ ግድያው ፥ ጫጫታው ፥ ሁካታው ጸጥ አለ ። ምሽጉና ሕንጻው ዐወታደሮቹ ቁጥጥር ሥር ሆኑ ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ በኋላ ፀአካባቢው ባሉት ሕንጻዎች ውስጥ የተሸሸጉ አመጸኞች ይኖሩ ይሆናል በማለት መታደሮቹ የአካባቢውን ሕንጻዎች ያስሱ ጀመር ።

— 5 —

ማሪዩ በጥይት ተመትቶ ፣ ሕሊናውን ስቶ ሲወድቅ በላዩ ላይ ሲያርፍ የተሰማው የሰው እጅ የግሮን ቫልግ እንጂ የመታደሮቹ አልነበረም ። ግሮን ቫልግ በውጊያው በተጥታ ተካፋይ አልሆነም ። የሱ የሥራ ድርሻ ቆስለው የወደቁትን ማንሳትና ወደ ሕክምናው ክፍል መውሰድ ነበር ።

ማሪዩ ተመትቶ ሲወድቅ ግሮን ቫልግ እንዶነብር ዘልሎ ሔዶ አነሳውና ተሸክሞት ወደ ኋላው አፈገፈገ ። በዚያ ወቅት እነ ኤንጉርልራና መታደሮቹ በመጠጥ ቤቱ በር ግብግብ ገጥመው ስለነበረ ወደ ሕክምና መስጫው ክፍል በመሔድ ፈንታ ግሮን ቫልግ ማሪዩን እንደተሸከመ ወደ ሕንጻው ጓሮ ሠር አለ ። ቦስተጓሮ ያለው ቤታ ከተኩስ ነጻ ነበር ። ማሪዩን ግድግዳውን አስደግፎ መሬት ላይ አኖረውና አካባቢውን ይታኝ ጀመር ። ወዲ አነስተኛው ምሽግ እቅጣጫ ቢመለከት ከውጭ የመታደሮች ስልፍ ይታያል ። የመንግሥት መታደሮች ዋናውን ምሽግ ብቻ ሳይሆን አነስተኛውንም ጭምር ከብበውታል ። መውጫ ቀዳዳ ፣ ማምለጫ በር የለም ። ግሮን ቫልግ ጭንቅ ብሎት እንደገና አካባቢውን ይታኝ ጀመር ።

ምንም ስማድረግ እንደማይቻል ሲገነዘብ ግሮን ቫልግ መሬት መሬቱን ይመለከት ገባ ፣ መሬቱን በዓይኑ ቅጥር ለማምለጥ እንደፈለገ ሁሉ ። እንዲሁ መሬት መሬቱን ሲመለከት ሳለ ከአነስተኛው ምሽግ ሥር በዘር ሃራ ብረት የተከደነ ጉድጓድ መኖሩን ልብ አለ ። ክዳኑ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሆኖ ርዝማኔውም ወርዱም እኩል ነው.....እያንዳንዱ ሁለት ሜማ ። ዙርያውን ያቅፉት ድንጋዮች ተቆፋፍረው ሳሊተዋል ። ግሮን ቫልግ ወደዚያ ሔድ ብሎ ድንጋዮቹን ገፋ ገፋ አድርጎ ዘርዛራውን ብረት ነቅሎ አነሳው ። ከዚያ በኋላ ወዲ ማሪዩ ተመልሶ ፣ ተሸክሞት መጣና ጉድጓዱ ውስጥ ገባ ። ሦስት ሜትር ያህል ከወረዱ በኋላ እግሩ መሬት ነካ ። በከርሰ ምድር ውስጥ ካለ መተላለፊያ በረንዳ የደረሰ መስሎም ተሰማው ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሁለት

የፓሪስ ከርሰ ምድር

— 1 —

የፓሪስ ገጸ ምድር ቀጥ ያሉ መንገዶች ፣ ተዳፋራ መንገዶች ፣ ዝግ መንገዶች ፣ ክፍት መንገዶች ፣ ወዘተርፈ እንዳሉት ሁሉ ከርሰ ምድሩም ቀጥ ያሉ ፣ የተጠማዘዙ ፤ የተወሳሰቡ ፣ መተላለፊያ በረንዳ የመሳሰሉ መንገዶች አለት ። እነዚህ መንገዶች የውሃ ፍሳሽ መውረጃዎች ናቸው ። ከተማው እየተስፋፋ በሔደ ቁጥር የፍሳሽ መውረጃዎችም በዚያው መጠን እየተስፋፉ ይሔዳሉ ። በ1832 ዓ. ም. የፍሳሹ መንገዶቹ ጠቅላላ ርዝማኔ 226,610 ሜትር ነበር ።

የፍሳሽ መውረጃዎቹ ርጥበት አይለያቸውም ። በራድ ናቸው ። ይሸ ትታሉ ። ጨለምላማ ናቸው ። አይጦች ይራቡባቸዋል ። ከሰ አውላቂዎችና ወንጀለኞችም ይደበቁባቸዋል ።

ዣን ቫልዣ የገባበት ጉድጓድ ወደ ከርሰ ምድር ከሚያስገቡ በርካታ መግቢያዎች አንዱ ነበር ። ጭለማው ፣ ዝታው ፣ ጸጥታው ግር አሰኝቶት ዝም ብሎ ቆየ ዣን ቫልዣ ። ምንም አልታይህ አለው ። ምንምም አልሰማ አሰው ። እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ ቢደባበስ መተላለፊያው በረንዳ ጠባብ ሆኖ አገኘው ። በአግሩ ሥር ያለው መሬት ርጥብ ነው ። ጉድጓድ ወይም አደናቃፊ ነገር ይኖራል ብሎ በማመን ቀስ ብሎ ይራመድ ጀመር ።

ጥቂት ደቂቃዎች ካለፉ በኋላ ሳይኖቹ ከጭለማው ጋር ተለማመዱ ። ከጉድጓዱ አፍ የሚገባም የብርሃን ጭላንጭል ነበር ። ዣን ቫልዣ ወደፊት እየገፋ ሲሄድ ግን የብርሃኑ ጭላንጭል ፈጽሞ ጠፋ ። ዣን ቫልዣ ፈራ አለ ። ይሁን እንጂ ወታደሮቹ ጉድጓዱ ውስጥ ሲገባ ምናልባት እይተውት እንዳይከተሉት ስለ ሰጋ መንገዱን ቀጠለ ።

አምሳ እርምጃ ያህል ከተራመደ በኋላ ጉድባ የመሰለ ነገር ስላጋጠመው ቆም አለ ። የመጣበትም መንገድ ከዚያ አልቆ ወደ ግራ ወይም ወደ

@OLDBOOKSPDF

ቀኝ የሚያስኬዱ ሁለት አማራጭ መንገዶች መኖራቸውን ተገነዘቡ ። «የትኛውን ልምረጥ?» ሲል አሰበ ጎን ቫልጣ ። ወደ ግራ የሚያመራው መንገድ ዘቅዘቅ ብሎ የሚወርድ በመሆኑ ወደ አንድ ወንዝ የሚዘልቅ ሳይ ሆን አይቀርም ሲል ገመተ ጎን ቫልጣ ። በእርግጥም ወደ ሴን ወንዝ የሚ ያመራ ነበር ። የሴን ወንዝ አካባቢ ሰው የሚበዛበት ሥፍራ ስለሆነ ጎን ቫልጣ ወደዚያ ለመሔድ አልፈለገም ። ፖሊሶችም በብዛት ይገኙበታል ። ስለሆነም ያንን መንገድ ትቶ ከፍ ከፍ ብሎ የሚሄደውን ቀኙን መንገድ ያዘ ። ጭለማው እየከበደ ሄደ ። ሆኖም ጎን ቫልጣ ሕያው ነው ወይም ሙት የማይባለውን ማሪዩን እንደተሸከመ ቀስ ብሎ ማዝገሙን ቀጠለ ። እንዲሁ ሲጓዝ ሳለ የሚወርድ ውሃ ካለበት ሥፍራ ደረሰ ። ውሃውን እያንቦራጨቀ እየገፋ ሔደ ጎን ቫልጣ ። መንገዱም በዚህ ጊዜ አዘቅዝቆ መውረድ ጀመረ ።

ጎን ቫልጣ ለማሸሽ ሰዓት ያህል ከተጓዘ በኋላ ድምጽ ሰማ ። ድምጹ ከውጭ የመጣ እንጂ ከከርሰ ምድሩ የመነጨ አልነበረም ። በገጸ ምድሩ ላይ እየተሸከረከሩ የሚያልፉ የተሸከርካሪዎች ድምጽ ነበር ። ቀጥሎም የገዛ ራሱ ጥላ ታየው ። ደንገጥ ብሎ ዞሮ ቢመለከት ከሩቅ የፋኖስ መብራት መኖሩን ተገነዘበ..... የፖሊስ ፋኖስ ። ከመብራቱ በስተኋላም ስምንት ወይም አሰር የሚሆኑ ቅርጾች ውርውር ሲሉ ታዩት ።

ያን ቀን ፣ ማለት ሰኔ 6 ቀን 1832 ዓ.ም. የመንግሥት ወታደሮች አመጸኞቹን ከተማው ውስጥ እያደኑ እንዲይዙ ፣ ፖሊሶችም ከርሰ ምድሩን እንዲያስሱ ታዝዘው ነበር ። ከርሰ ምድሩን የሚያስሱት በሦስት ቡድን ተመድበው ፤ አንደኛው በቀኝ ክንፍ ፣ ሁለተኛው በግራ ክንፍ ፣ ሦስተኛው በማዕከር ሆነው እንዲፈትሹ ተደርጎ ነበር ።

ፋኖስ ይዘው በጎን ቫልጣ አቅጣጫ ሲያመሩ የነበሩት ፖሊሶች የቀኙ ክንፍ ፈታሾች ነበሩ ። ፖሊሶቹ ወደ ጎን ቫልጣ አቅጣጫ ያመሩት እሱን አይተውት ሳይሆን ኮቴውን በሩቁ በመስማታቸው ነበር ። እሱም ፋኖሳቸውን በሩቅ አይቶ ጥላ ሲይዝ የኮቴው ድምጽ ጠፋ ።

የኮቴው ድምጽ ሲጠፋባቸው ፖሊሶቹ ቆም ብለው ይመካከሩ ጀመር ። ቀደም ብለው የሰሙት ድምጽ ፈጽሞ ስለጠፋባቸው ጀሮአቸው ያልሆነ ነገር ያሰማቸው መስሎ ታያቸው ። ጎን ቫልጣ ባለበት አቅጣጫ መሄድም ዋጋ የሌለው ከንቱ ድካም መስሎ ታያቸው ። በምክክራቸው መጨረሻ ወደ ግራ ታጥፈው እንዲያመሩ ወሰኑ ። ይሁን እንጂ ተከፋፍለው ግማሾቹ ወደ ግራ ፣ የተቀሩት ወደፊት ቢቀጥሉ ኖሮ ጎን ቫልጣን ባገኙት ነበር ። እነሱ ግን መከፋፈሉን ትተው ወደግራ በሚወስደው መተላለፊያ ለመሄድ ወሰኑ ። ጎን ቫልጣ በአጋጣሚ ዳነ ። የፖሊሶቹም የፋኖስ መብራት ከዓይኑ ተሰወረ ።

ይህም ሆኖ ሳለ የቡድኑ መሪ ወደ ግራ ተጠምዞ ከመሔዱ በፊት ሕሊናውን ለማሳረፍ ያህል ጠመንጃውን ጎን ቫልጣ በሔደበት አቅጣጫ

@OLDBOOKSPDF

ተኰሰው ። የተኩሱ ድምጽ የገደል ማሚቶ ሆኖ አስተጋባ ። ጥይቱም የመ
ተላለፊያውን በረንዳ ጣራ መትቶ ቅርፊት የመሰለ ነገር ከጣራው ተገሸለጠ
ወደቀ ። ግን ቫልግ ግን አልተመታም ።

ተኩሱና የገደል ማሚቶው ርጭ ሲል ጸጥታው ጥልቀት አገኘ ። ጭስ
ማውም ከበፊት ይልቅ ከበደ ።

ግን ቫልግ ከድንጋጤው የተነሳ ጆሮውን አቁሞ እያዳመጠ ፣ ዓይኑን
በልጦ እየተመለከተ ግድግዳውን የመጥኛ ብሎ ለረጅም ጊዜ ሳይነቃነቅ
ባለበት ቆየ ።

— 2 —

በሰላም ጊዜ ብቻ ሳይሆን በአመጽ ወቅትም ቢሆን የፓሪስ ፖሊሶች
የየዕለት ግዳጃቸውን ከመፈጸም ፣ ተራ ወንበዴዎችን ከመከታተልና የሕ
ብረተሰቡን ደህንነት ከመጠበቅ ወደ ኋላ አይሉም ነበር ። ያን ቀንም ፣
ሰኔ 6 ቀን 1832 ዓ.ም. ረጅም ካፖርት የለበሰ አንድ የፖሊስ ባልደረባ
በሴን ወንዝ አካባቢ አንድ ተራ ወንበዴን ሲከታተል ነበር ። ወንበዴው
መናኛ ኮት ለብሷል ። ፖሊሱ እንደተከተለው አውቆ ፊት ፊት ቀድሞ ይሸ
ሻል ። ፖሊሱ ወንበዴውን ለማዘናጋት አስቦ ፣ የተከተለው እንዳይመስል
ዘና ብሎ ይከታተለዋል ። አንድ ጋሪ ነጂ ደሞ ከፖሊሱ ጋር ምንም ግንኙ
ነት የሌለው አስመስሎ ዝግ ባለ እርምጃ ጋሪውን እየነዳ ይከተለዋል ።
ይሁን እንጂ ፖሊሶች ለአስቸኳይ ጉዳይ ተሽከርካሪ አስከትለው እንደሚ
ጓዙ የታወቀ ነው ።

ፖሊሱ ለጋሪ ነጂው የእጅ ምልክት ሲያሳየው ባለጋሪው ቀረት ብሎ
ይከተለው ገባ ። ፖሊሱ ለጋሪ ነጂው የእጅ ምልክት መስጠቱን በመሸሽ
ላይ ያለው ወንበዴ አያውቅም ።

እንዲሁ እየተከተሉት ሲሔዱ ሳሉ ወንበዴው የቁሻሻ ክምር ካለበት
ሥፍራ ደርሶ ወደክምሩም በስተጀርባ ዞር ብሎ ከፖሊሱ ዓይን ተሰወረ ።
ፖሊሱ በዚህ ጊዜ ርምጃውን አፋጠነው ። የቁሻሻው ክምር ካለበት ደርሶ
ወንበዴውን በዓይኑ ቢፈልገው አልታይህ አለው ። «ወዴት ገባ? መሬት
ዋጠችው ወይንስ ሴን ወንዝ ውስጥ ዘልሎ ገባ?» ብሎ ያሰብ ጀመር ።

እንዲሁ እያሰበ ዙርያ ገቡን በዓይኑ ሲመረምር በዘርዛራ ብረት የተ
ከደነ ጉድጓድ መኖሩን ልብ አለ ። ግን ቫልግ ተደብቆ የገባበት ዓይነትና
ወዴ ከርሰ ምድር የሚያስገባ ጉድጓድ ነበር ። ፖሊሱ ጐንበስ ብሎ በእጁ
ቢሞካክረው ዘርዛራው የብረት ክዳን ጥብቅ ነው ። ደሞም በቁልፍ ተቆል
ፏል ። «ወንበዴው ቁልፉን ከወዴት አግኝቶ ከውስጥ ሆኖ ቆለፈው?»

@OLDBOOKSPDF

ሲል በጣም ተገረመ ፖሊሱ ። ያም ሆነ ይህ ወንበዴው ተመልሶ ሳይወጣ አይቀርም ፣ አስዚያም ሌላ ሰው መጥቶ ከዚያው ጉድጓድ ሲገባ አያለሁ በሚል ተስፋ ከቁሻሻው ክምር በስተጀርባ ሆኖ ይጠባበቅ ጀመር ።

— 3 —

ፖሊሱና ወንበዴው በዚህ ሁኔታ ባለበት ወቅት ግን ቫልጣ የከርሰ ምድር ጉሠውን ቀጠለ ። የት እንዳለና ወዴት እንደሚያመራ አያውቅም ። በጣም ርቦታል ። ድክምክምም ብሎታል ። መተላለፊያው በረንዳ በሰው ቁመት ልክ የተሠራ ቢሆንም ማሪዩን ከበረንዳው ጣራ እንዳያጋጨው በመፍራት ጐንበስ ብሎ ነበር የሚራመደው ።

ለረጅም ጊዜ ከተጓዘ በኋላ መተላለፊያው በረንዳ ሰፊ ከሆነበት ሥፍራ ደረሰ ። ይህ ሰፊ በረንዳ በሁለት አቅጣጫ የሚያስኬድ ነበር ። አንደኛው አዘቅዝቆ ይወርዳል ። ሁለተኛው ከፍ ከፍ እያለ ይሔዳል ። እያዘቀዘቀ የሚወርደው ወደ ሲን ወንዝ የሚያደርስ ነበር ። ግን ቫልጣ የትኛውን መንገድ ብመርጥ ይሻለኛል ሲል አሰበና አዘቅዝቆ የሚወርደውን መረጠ ። ይኸውም በንሲብ አንጂ የተሻው ወደት እንደሚያመራ በማወቅ አይደለም ።

ድካሙ ያለልክ ሲበረታበት የጸሐይ ብርሃን ጭላንጭል ካሰበት ሥፍራ ደርሶ ቆም ብሎ ማሪዩን ከጀርባው አውርዶ ከፍሳሹ ዳርቻ አኖረው ። የማሪዩ ዓይኖች እንደተዘጉ ናቸው ። ጸጉሩ ከራሱ ጋር ተጣብቋል ። እጅቹ ሙትት ብለዋል ። ሸሚዙ ከቁስሉ ውስጥ ገብቶ ተጣብቋል ።

ግን ቫልጣ እጁን ከማሪዩ ደረት ሰድዶ ቢያየው ማሪዩ አልሞተም ። ልቡ ይመታል ። ግን ቫልጣ ሸሚዙን ቀድዶ የማሪዩን ቁስል በተቻለው መጠን አሰረሰት ። ይሙም እንዲቆምለት የተቻለውን ጥረት አደረገ ። ከዚያም በኋላ በብርሃን ጭላንጭል ፊቱን አስተዋለውና የመረረ ጥላቻ አደረበት ።

ግን ቫልጣ የማሪዩን ልብሶች ነካክቶ ሲያያቸው በኪሱ አንድ ዳቦና የማስታወሻ ደብተር መኖራቸውን ተገነዘበ ። ዳቦው በትናንትናው ዕለት ማሪዩ ገዝቶት ኪሱ ውስጥ የረሳው ነበር ። ግን ቫልጣ ረሀቡን ለማስታገስ ዳቦውን ጐራረሰና የማስታወሻ ደብተሩን ከፍቶ ተመለከተው ። በመጀመሪያው ገጽ ማሪዩ ጽፎ ያስተረውን ማስታወሻ አይቶ አነበበው ፣— «ስሜ ማሪዩ ፖሚርሲ ይባላል ። አሰከሬኔን ወደ አያቴ ዘንድ ውሰዱልኝ ። አያቴ ጊልናርማ በሬይ—ዱ—ካልቨር ጐዳና በቁጥር 6 ሕንጻ ውስጥ ይኖራል ።»

@OLDBOOKSPDF

ጐን ቫልጣ ጽሑፉን ካነበበው በኋላ የማስታወሻ ደብተሩን ወደነበረበት መለሰው ። ዳቦውን ከበላ በኋላ ኃይሉ መለስ ስላለት ሚሪዬን አንስቶ ተሸከመውና ጉዞውን ቀጠለ ።

— 4 —

በብረታኛ ወይም በእስኮትላንድ የባሕር ጠረፍ አካባቢ የሚገዝ ሰው ሳያውቀው መሬመድ የሚቸግረው ጊዜ እንዳለ ይነገራል ። አሸዋው እግሩን ያዝ ያደርገዋል ። የረገጠው ሥፍራ በውሃ ይሞላል ። በተራመደ ቁጥር የገዛ እግሩ ይከብደዋል ። ቀጥሎም እግሩ መስመጥ ይጀምራል ። ስቦ ሊያወጣው ሲሞክር የባሰውን ወደ ውስጥ ይስጥማል ። አሸዋው ከቁርጭምጭሚቱ ይደርሳል ። ቀጥሎም ከቅልጥሙ.....ከጉልበቱ ። ማጥ ውስጥ መግባቱን ተገንዝቦ ይሸበራል ። የተሸከመው ነገር ካለ ይጥለዋል ። ይጮሃል ። እርዳታ እንዲያገኝ ይማጸናል ። የሚረዳው ሰው ግን አያገኝም ። ቀስ በቀስ መስመጡን ይቀጥላል ። ማጡ እስከወገቡ ይደርሳል ። ቀጥሎም እስከ አንገቱ.... እስከ ጭንቅላቱ ። ጩኩ ብቻ ይቀራል ። ቀጥሎም ጸጉሩ ይሰምጥና ሰውዬው በቁመናው ይቀበራል ። አይጣል..... አያድርስ የሚያሰኝ አሟሟት!

የአሸዋ ማጥ እንዳለ ሁሉ በፓሪስ ከርሰ ምድር ውስጥ የፍሳሽ ማጥም አለ ። የያዘ እንደሆነ ስቃዩ ከአሸዋ ማጥ ይበሳል ። በአሸዋ ማጥ የሚሞት ሰው ንጹህ አየር እየተነፈሰ ፣ የጸሐይ ብርሃን እያየ ሲሆን በፍሳሽ ማጥ የሚሞት ሰው ግን በሳይነ ምድር ሽታ የተበከለ አየር እየተነፈሰ በጭለማ ውስጥ ሆኖ ነው ሕይወቱ የምታልፈው ።

የማጥ ጥልቀት ከቦታ ቦታ ይለያያል ። ሦስት ወይም አራት ጫማ ጥልቀት ብቻ ሊኖረው ይችላል ። ስምንት ወይም አስር ጫማ ጥልቀት ሊኖረው ይችላል ። አለዚያም በጣም ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ ምን ያህል ጫማ ጥልቀት እንዳለው በውል ሳይታወቅ ይችላል ።

ጐን ቫልጣ ማጥ ካለበት ሥፍራ ደረሰ ። በሻንዜሊዜ ሥር የፍሳሽ ማጥ ማግኘት አዲስ ነገር አልነበረም ። በትናንትናው ማታ በወረደው ዶፍ ምክንያት ነበር ማጡ ሊኖር የቻለው ።

ጐን ቫልጣ ሲረማመድበት የነበረው ጠጣር መንገድ ከእግሩ ሥር እየሟሟ ሄደ ። ከውስጥ እንደጭቃ የተጋገረ ሆኖ ከላይ በውሃ የተሸፈነ ነበር ። ወደኋላው ሊመለስ አሰበ ጐን ቫልጣ ። ነገር ግን ተመልሶ ወዴት ሊሔድ? ወደመጣበት እንዳይመለስ የማይታሰብ ሆነበት ። ድክምክም ብሎታል ። ማሪዬም ጣዕር ላይ ነው ያለው ። ስለሆነም ወደፊት በመግፋቱ ቆረጠ ። ይበልጥ እየገፋ በሔደ ቁጥር ማጡ ይበልጥ ያስጥመው ጀመር ።

@OLDBOOKSPDF

የተጋገረው ጭቃ እስከቅልጥሙ ፥ ከሳይ ያለው ውሃ እስከጉልበቱ ደረሰ ። እሱ ግን መንገዱን ቀጠለ ። ጭቃው እስከጉልበቱ ፥ ውሃው እስከወገቡ ደረሰ ። አሁንም ወደፊት እየ·ሩ ሄደ ። ውሃው ከብብቱ ደረሰ ። በመስመጥ ሳይ መሆኑ ተሰማው ። መረማመድም እያቃተው ሔደ ። ያለ ኃይሉን ሰብስቦ መንገዱን ቀጠለ ። ውሃው ከአንገቱ ደረሰ ። ማሪዩን ግን ከፍ አድርጎ ይዞታል ። ከዚያ በኋላ መልካም ዕድል አጋጥሞት አማሩ ጠጣር ነገር ላይ አረፈ ። ትርይታ ተሰምቶት ጠጣሩ ነገር ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ ።

ግን ቫልጣ ከሞት አመለጠ ። ማጡን ከተሻገረው በኋላ በጉልበቱ ተንበርክኮ ጸለየ ። በልቡም ውስጥ ብርሃን አደረ ።

ከተንበረከከበት ተነስቶ እንደገና መንገዱን ቀጠለ ። ሙቶ እርምጃ ያህል ከተራመደ በኋላ የጭሳሹ መንገዱ የሚጠመዘዝበት ሥፍራ ስለነበረ ሳይገነዘበው ከግድግዳው ጋር ተጋጨ ። ዓይኑን አቅንቶ ቢያይ ከሩቅ ብርሃን አለ ፥ የጸሐይ ብርሃን ። ከከርሰ ምድሩ የሚያስወጣ በር መኖሩን ተገንዝቦ ወደዚያ አመራ ። ልቡ በአዲስ ተስፋ ስለተመላም ድካሙን ረሳው ። ሽክሙም የቀለለለት መሰለው ። እየገፋ በሔደ ቁጥር መንገዱ እየጠበበ ፥ መውጫው በር ደሞ ይበልጥ እየገላ ሔደ ።

ግን ቫልጣ ከመውጫው በር ያርሶ ቢመለከት በሩ በዘርዘራ ብረት ተዘግቶ ተቆልፏል ። ከበሩ ማዶ ገጸ—ምድር ነው ። ንጹህ አየር አለ ። ግን ቫልጣ ማሪዩን ከጀርባው አውርዶ ዘርዘራውን ብረት በሁለቱም እጅቹ ኀይል ኀይል አድርጎ ይሞክረው ገባ ። ነገር ግን ንቅንቅ አልል አለው ።

የመውጣት ተስፋው እንደገና ጨለሞበት «ምን ባደርግ ይሻለኛል?» ብሎ ያስብ ጀመር ። ወደመጣበት እንዳይመለስ የማይታሰብ ሆነበት ። ድካሙ ይህ ነው አይባልም ። የሰገራው ማጥ አለ ። ከፖሊሶችም ጋር ሊፋጠጥ ይችላል ። ስለሆነም የመመለሱን ሀሳብ ከአእምሮው አውጥቶ ጥሎ ጀርባውን ለመውጫው በር ሰጥቶ ከማሪዩ አጠገብ ቁጭ አለ ። ማሪዩ አሁንም ቢሆን እንዳችም ንቅናቄ አያሳይም ። እንደበድን ጸጥ ብሏል ።

ግን ቫልጣ ከሃሳብ ባህር ውስጥ ገባ ። የሚያስበው ግን ስለራሱ ወይም ስለማሪዩ ሳይሆን ስለኩዜት ነበር ።

በዚህ ሁኔታ እያለ የሰው እጅ ትከሻው ላይ አረፈበት ። «አካፍሰኝ!» የሚልም ድምጽ ሰማ ።

«ሕልም ውስጥ ነው ያለሁ—ት?» ብሎ ዓይኑን አቅንቶ ቢመለከት አንድ ሰውዬ በአጠገቡ ቆሟል ። ሰውዬው አልባሌ ልብስ ለብሷል ። ባዶ እግሩን ነው ። ኮቴው እንዳይሰማበት በማሰብ ጫማዎቹን አውልቆ በእጁ ይዟቸዋል ።

ሰውዬው ለግን ቫልጣ ዓይኖች እንግዳ አልነበረም ። ደህና አድርጎ ያውቀዋል ። ቱናርዲዬ ነበር ። ይሁን እንጂ ቱናርዲዬ ግን ቫልጦን ለይቶ

@OLDBOOKSPDF

አላወቀውም ። ይኸውም ጐን ቫልጐ ጀርባውን ሰበሩ ስጮ ፊቱን ወደ ጭለማው መልሶ ከመቀመጡም በላይ ፊቱ በደም ተሰውሶ ስለነበረ ነው ። በጭለማ ቀርቶ በብርሃን ቢያየው ኖሮ እንኳ ቴናርዲዬ ጐን ቫልጐን ሲይቶ ባላወቀው ነበር ።

«እንዴት አድርገህ ከዚህ ለመውጣት አሰብክ?» ሲል ጠየቀው ቴናር ዲዬ ። ጐን ቫልጐ መልስ አልሰጠውም ።

«ከዚህ መውጣት ቀላል አይምሰልህ!» አለውና ቴናርዲዬ ፣ «ከዚህ ለመውጣት ትፈልግ የለም?» ሲል ጠየቀው ።

«አዎን» አለው ጐን ቫልጐ ።

«እንግዲያው አካፍለኝ ።»

«ምን ማለትህ ነው?»

«ምን ማለቴ እንደሆነ አልገባህም?» አለውና ፣ «ይህንን ሰውዬ የገደልከው በከንቱ ሊሆን አይችልም ። ግንዘብ አለው ብለህ ነው የገደ ልከው ። እና ግንዘቡን አካፍለኝና በሩን ልክፈትልህ ። ቁልፉ በእጄ ይገ ኛል» አለው ።

ጐን ቫልጐ ይህን ሲሰማ የበፊት ጭንቀቱ ቀሰል አለለት ።

«እንካ ደሞ ግመድ» አለው ቴናርዲዬ ፣ ከኮቱ ኪስ ገመድ አውጥቶ ።

«ገመድ.....? ምን ያደርግልኛል?»

«ያደርግልሃል እንጂ! ገመድ ብቻ ሳይሆን ድንጋይም ያስፈልግሃል ። ድንጋይ ግን ከዚህ ስትወጣ የፈለግኸውን ያህል ታግኛለህ ።»

«ምን ልፈጥርበት?»

«ይህንን አስከሬን ወንዝ ውስጥ መወርወር ይኖርብሃል ። ከድንጋይ ጋር በገመድ አስረህ ካልወረወርከው አስከሬኑ ይንሳፈፍብሃል» አለውና አዲስ ሃሳብ እንደመጣለት ሰው ጣቱን አስጮሆ ፣ «እረ ለመሆኑ የፍሳሹን ማጥ እንዴት አድርገህ አለፍከው? እኔ ደፍሬ ልገባበት አልቻልኩም» ብሎ ፣ «አፍ.....! ሠገራ ሠገራ ትሸታለህ ኧል!» አለው ። ቀጠል አድርጎም ፣ «ለመሆኑ አስከሬኑን ማጡ ውስጥ ለምን አልጨመርከውም? ብቻ..... ጥሩ አድርገሃል ። ማጡ ውስጥ ብትጨምረው ኖሮ ምናልባት የፍሳሽ ሠራተ ኞች ያገኙት ነበር ። ካገኙት ደሞ ክትትል ተደርጎብህ ትያዝ ነበር ። አስከ ሬኑን ወንዝ ውስጥ ብትጨምረው ግን አስከአንድ ወር ድረስ ሳይገኝ ይሰነ ብታል ። ከዚያ በኋላ ቢገኝ እንኳ ማን ገደለው ብሎ የሚጠይቅ አይኖርም ። ስለዚህ ጥሩ አድርገሃል» አለው ፣ ጐን ቫልጐ ማሪዬን ሆን ብሎ ግንዘቡን ፈልጎ ገድሎታል ብሎ በማመን ። ጐን ቫልጐ ግን ለዚህ ሁሉ መልስ አልሰጠውም ።

@OLDBOOKSPDF

ቴናርዲዬ የጣን ቫልጣን ትከሻ ነቅንቅ ኢያደረገ ልጥለፉውን ቀጠለ ፤ «በል እንግዲህ ለጉዳዩ እልባት እናብጅለት..... የበሩ ቁልፍ ይኸውና..... አንተ ደሞ ገንዘቡን አሳየኝና እኩል አካፍለኝ» አለው ።

ቴናርዲዬ ይህንን ሁሉ የሚለፈልፈው ዝቅ ባለ ድምጽ ነበር ፤ ሴላ ሰው እንዳይሰማው የፈራ ይመስል ። ካለነሱ በስተቀር ሴላ ሰው ግን አልነበረም። ጣን ቫልጣ በበኩሉ ፥ «ምናልባት ጭለማው ውስጥ የተደበቁ ሌሎች ወን በዴዎች ይኖሩ ይሆናል..... ቴናርዲዬ ዝቅ ባለ ድምጽ የሚለፈልፈው አነሱ እንዳይሰሙትና ገንዘቡንም እንዳይካፈሉት በመፍራት ይሆናል» ሲል አሰበ።

«ለጉዳዩ እልባት እናብጅለት ብዬሃለሁ» አለው ቴናርዲዬ ፤ «እና ከገ ደልከው ሰውዬ ኪስ ምን ያህል ገንዘብ አገኘህ» ሲል ጠየቀው ።

ጣን ቫልጣ ኪሱን ደባብሶ ሠላሳ ፍራንክ አውጥቶ አሳየው ። ቴናር ዲዬ ገንዘቡ ይህ ብቻ ይሆናል ብሎ አላመነም ። «ለዚህ ብለህ ነው የገደልከው? አስቲ አናያለንህ» ብሎ የጣን ቫልጣንና የማሪዩን ኪስ ይፈትሽ ገባ ። ጣን ቫልጣ አልተቃወመውም ። ገም ብሎ ተፈተሸለት ።

የማሪዩን ኮት በሚፈትሽበት ጊዜ ቴናርዲዬ ከኩቱ ብጣሽ ጨርቅ ቀድዶ አወጣለት ። ጣን ቫልጣ ይህንን ልብ አላለም ። ብጣሹን ጨርቅ ቀድዶ ያወጣለት ምናልባት መደፊት ሚቹ ማን እንደሆነ ምርመራ በሚደረ ግበት ጊዜ እንደማስረጃ ሊቀርብ ይችላል ብሎ በማሙን ሳይሆን አይቀርም ። ቁራጩን ጨርቅ ኮቱ ኪስ ውስጥ ጨመረው ።

ፍተሻውን ሲያበቃ ፤ «አውነትም ይኸው ብቻ ነው ያለህ» ብሎ ሠላሳ ውን ፍራንክ ኪሱ ውስጥ ጨመረው ። «ለሠላሳ ፍራንክ ብለህ ሰውን መግ ደልህ ግን.....» አሰና ፤ «ለማንኛውም አሰፈላጊውን ስለከፈልህ አሁን ልት ወጣ ትችላለህ.....» አለው ።

ጣን ቫልጣ ማሪዩን አንስቶ ተሸከመው ። ቴናርዲዬም ቀስ ብሎ እየ ተራመደ ወደ መውጫው በር ጠጋ ብሎ ፥ ከዘርዛራው ብረት ባሻገር በጥር ጣሬ ዓይን ወደ ውጭ ተመልክቶ ሲያበቃ በሩን ከፈተለት ። ጣን ቫልጣ ወደ ገጸ ምድር ወጣ ። ቴናርዲዬም በሩን መልሶ ቆለፈውና በከርሰ ምድሩ ውስጥ ቀረ ። ጭለማው ዋጠው ።

— 5 —

ጸሐይ ጠልቃለች ። ጊዜው ደንገጎገ ብዓል ። የሴን ወንዝ ይንሿ ሿል ። ከዋክብት ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል ።

@OLDBOOKSPDF

ጎን ቫልጎ ማሪዩን መሬት ላይ አውርዶት የሕሊና ጸሎት አደረገና ከወንዙ በእፍኙ ውሃ አፍሶ ማሪዩ ሬት ላይ አርከፈከፈው ። የማሪዩ ዓይኖች አልተከፈቱም ። ይሁን እንጂ አሁንም ይተነፍሳል ።

ጎን ቫልጎ እንደገና በእፍኙ ውሃ ለማፈስ ጐንበስ ሲል ከበስተጐላው አንድ ሰውዬ መጥቶ ቆም አለ ። ረጅም ነው ሰውዬው ። ካፖርት ለብሷል ። ቆመጥ ይሏል ። ክንዶቹን ደረቱ ላይ አነባብሯቸዋል ። ጎን ቫልጎ ቀና ብሎ ቢመለከት ጎቬር ነው ።

ጎቬር ቀደም ብሎ ቴናርዲዬን ሲከታተል ነበር ። ቴናርዲዬ ከርሰ ምድሩ ውስጥ ገብቶ ከተሰወረበት በኋላ ከአሁን አሁን ይወጣል ብሎ ሲጠባ ቢቀው ነበር ። ቴናርዲዬም የከርሰ ምድሩን በር ከጥቶ ጎን ቫልጎን ያስ ወጣው ለገንዘቡ ብቻ ብሎ ሳይሆን የጎቬርን መንፈስ ከራሱ አርቆ በጎን ቫልጎ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ነበር ።

ጎን ቫልጎ በደምና በእድፍ ተበክሎ ስለነበረ ስጊዜውም ቢሆን ጎቬር ሰይቶ ሊያወቀው አልቻለም ።

«ማን ነህ?» አለው ረጋ ባለ ድምጽ ።

«እኔ ነኝ» አለው ጎን ቫልጎ ።
«አንተ ማን?»
«ጎን ቫልጎ ።»
ጎቬር ጠጋ ብሎ እጅጉን ጎን ቫልጎ ትከሻ ላይ አሳርፎ አትኩሮ አየው ። አሁን ገና አሉ መሆኑን ተገነዘበ ።

«ተቆጣጣሪው ጎቬር.....» አለው ጎን ቫልጎ ፤ «ይሽው አግኝተሃኛል ። በመዳፍህ ሥር አስገብተሽኛል ። ደሞም ባፌ ጠዋት አድራሻዬን ስለጥህ እንደምትከታተለኝ አውቅ ነበር ። እና አሁን ልትይዘኝ ትጉላለህ። ይህንን ከሚድረግህ በፊት ግን አንድ ነገር ብትፈቅድልኝ.....»

ጎቬር ሃሳብ ውስጥ ገብቶ ትንሽ ቆየና ፤ «እዚህ ምን ታደርጋለህ? ይህ ሰውዬስ ማን ነው?» ሲል ጠየቀው ።

«ይሽንኑ ሰውዬ በሚመለከት ጉዳይ ነው አንድ ነገር ብትፈቅድልኝ ያልከህ» አለው ጎን ቫልጎ ፤ «እኔን የፈለግሽውን ልታደርገኝ ትችላለህ ። ከዚያ በፊት ግን ይሽንን ሰውዬ ወደቤቱ እንዳደርሰው ብትፈቅድልኝ.....»

ጎቬር እምቢ ብሎ አላሳፈረውም ። ጎን ቫልጎም ጐንበስ ብሎ መሐረብ ከኪሱ አውጥቶ ውሃ ነክረውና የማሪዩን በደም የተበከለ ግምባሩን ጠረገለት ።

@OLDBOOKSPDF

«ይህ ሰውዬ ምሽጉ ውስጥ ነበር ። ማሪዩ ብለው ሲጠሩት የነበረው ነው» አለው ዣን ቫልዣ ።

ገርቬር የማሪዩን እጅ ያዝ አድርጎ የደም ምቱን መረመረውና «ሞታል!» አለው ።

«ቆስሏል እንጂ አልሞተም!» አለው ዣን ቫልዣ ።

«እና ከምሽጉ አንስተህ ነው እዚህ ያመጣኸው?»

ዣን ቫልዣ መልስ አልሰጠውም ። ዝም ብሎት ትንሽ ቆየና ፤ «በፊይ—ዱ—ክልቬር ጐዳና ከአያቱ ጋር ነው የሚኖረው» ብሎ ማሪዩ ጽፎ ያስቀረውን ማስታወሻ አሳየው ።

«ባለ ጋሪ!» ሲል ተጣራ ገርቬር ።

ባለ ጋሪው ጠጋ ሲል ማሪዩን አንስተው በኋለኛው መቀመጫ አኖሩት ። ገርቬርና ዣን ቫልዣ በፊተኛው መቀመጫ ተቀመጡ ።

ጋሪው ተንቀሳቅሶ በባስቲይ አቅጣጫ በኩል ያመራ ጀመር ። በተንጣ ሜገጨ ቁጥር ከማሪዩ ቁስል ደም ይንጠባጠባል ። ከፊይ—ዱ—ክልቬር ጐዳና ፥ ቁጥር 6 ሕንጻ ደርሰው ጋሪው ሲቆም ገርቬር ቀድሞ ወረደ ። ሐኪ ብሎ የምድረ ግቢውን በር አንኳኳው ። በረኛው እያዛጋ ብቅ አለ ። የበራ ሻማ በእጁ ይዟል ።

«ይህ ቤት ጉርልኖርማ የሚባል ሰው ቤት ነው?» ሲል ገርቬር ቦረኛውን ጠየቀው ።

«ነው..... ለምን ፈለጓቸው?»
«ልጁን ይዘን መጥተናል ።»
«ልጁ.....ን?»
«አዎን ። ልጁ ወደ አመጸኞች ምሽግ ሐዱ የሆነውን ሆኗል ።»
«ወደ አመፀኞች ምሽ.....ግ?»
«አዎን ። ሐደሀ አባቱን ቀስቅሰው ።»

በአመጹ ምክንያት ጉርልኖርማና መላው ቤተሰቡ በጊዜ ተኝተው ነበር ።

በረኛው ጉርልኖርማን ሳይሆን ኂኬትን ቀሰቀሳት ። ኂኬት በበኩሏ ማድሚዜል ጉርልኖርማን ቀሰቀሰቻት ።

ማሪዩን ከጋሪው አውርደው ወደ አንደኛው ፎቅ አውጥተው ከእን ግዳ መቀበያው ክፍል ወዲህ ባለው አንስተኛ ክፍል ውስጥ ሶፋ ላይ አኖ ሩት ። ወዲያውኑ ባስክ ፥ ወንዱ ሠራተኛ ሐኪም ፍለጋ ሐዱ ። ገርቬርና ዣን ቫልዣ ግን በዚያ አልቆዩም ። ያረጀውን ወርደው ጋሪው ላይ ወጡ ።

@OLDBOOKSPDF

«ተቆጣጣሪው ግርቬር..... አንድ ሌላ ነገር ብትፈቅድልኝ.....» አለው ግን ቫልግ ።

«ምንድነው እሱ?» ሲል ጠየቀው ግርቬር ከረር ባለ ድምጽ ።

«ለአንድ አፍታ ወደቤቱ እንድመለስ ብትፈቅድልኝ..... ከዚያ በኋላ የፈለግኸውን ታደርግልኛለህ ።»

ግርቬር ዓይኑን ወደ ጋሪ ነጂው አዙሮ ፣ «ወደ ሉም አርሚ ጐዳና ንዳ..... ቁጥር 7 ሕንጻ» አለው ።

— 6 —

ግን ቫልግ ወደ ቤቱ ለመድረስ የፈለገው የኮዜትን ልብ ለማረጋጋት ፣ ማሪዩ የት አንዳለ ሊነግራትና አስፈላጊ የሆነውንም ሁሉ ለማጠናቀቅ ነበር ። እንደገና በግርቬር እጅ ከወደቀ በኋላ ማምለጫ ይኖረኛል ብሎ ለአንድ አፍታ እንኳ አላሰበም ። በግርቬር እጅ መልሶ የወደቀው ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ምናልባት የራሱን ሕይወት ለማጥፋት መከራ ባደረገ ነበር ። ግን ቫልግ ግን አቡነ ማሪዬልን ከወቀና ሕይወቱን ከሰወጠ ወዲህ እንዲህ ያለውን ድርጊት ለመፈጸም ጥርጥ ሊያስበውም አይችልም ነበር ።

ጋሪው ተጉዞ ተጉዞ ከሉም አርሚ ጐዳና ሲገባ መንገዱ ስለጠበበ አልፎ ለመሔድ አልቻለም ። ስለሆነም ጋሪው ቆሞ ግርቬርና ግን ቫልግ ከጋሪው ወረዱ ።

«መሲ ተቆጣጣሪ.....» አለ ባለጋሪው ግርቬርን እያየ ፤ «ዋጋቹ ደምና የኔዳዬ ጭቃ ጋሪዬን አቆሽሸው።ኛል ። የመቅመጫው ጨርቅ በደምና በጭቃ ስለተለወሰ ለማሳጠቢያ የሚሆን ካሣ እንዲከፈለኝ ይገባል ። ደሞም ከወንጀሉ ንጹህ መሆኔን የሚያረጋግጥ ማስታወሻ ጽፈው ቢሰጡኝ.....» አለው ።

በጋሪ ነጂው ዓይን ማሪዩ ተገዳይ ፣ ግን ቫልግ ገዳይ ናቸው ።

«ለከሣው ብቻ ሳይሆን ለኪራዩና ስጠበቅህበት ሰዓት ምን ያህል እንዲከፈልህ ትፈልጋለህ?» አለው ግርቬር ።

«ሰባት ሰዓት ተኩል ነው ከእርስዎ ጋር የቆየሁት ። ደሞም የጋሪዬ ጨርቅ አዲስ ስለሆነ በጠቅላላው ስሜንያ ፍራንክ ቢከፍሉኝ.....»

ግርቬር የጠየቀውን ከፍሎ አሰናበተው ። ከወንጀሉ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስታወሻ እንዲጽፍለት ያቀረበለትን ጥያቄ ግን ችላ አለው ።

@OLDBOOKSPDF

ጣን ቫልጣና ጣቪር ቀሪውን መንገድ በእግር ተጉዘው ከቱጥር ሰባት ሕንጻ ሲደርሱ ጣን ቫልጣ የመግቢያውን በር አንኳኳው ። በረኛው ከፈ ተለት ።

«በል ደርሰህ ና..... እኔ እዚሁ ሆኜ እጠብቅሃለሁ» አለው ጣቪር ። ጣን ቫልጣ በመገረም ዓይን አየው ። «እንዴት አምኖ ብቻዬን ይሰቀ ኛል.....? ወይንስ ከአሁን ወዲያ የት አባቱ ያመልጠኛል ብሎ ነው?» ሲል አሰበ ጣን ቫልጣ ።

ወደ ውስጥ ገብቶ ያረጀውን ወጥቶ ከእንደኛው ፎቅ ሲደርስ ቆም አለ ጣን ቫልጣ ። በእንደኛው ፎቅ ያለው መስኮት ክፍት ነበር ። ውጪ ከዚያ ይታያል ። ጣን ቫልጣ ያሰበውን አስቦ ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ ወደ ውጭ ተመለከተ ። ጣቪር ከነበረበት ቦታ አልነበረም ። እንቆቅልሽ ሆነበት ለጣን ቫልጣ!

— 7 —

ጣቪርና ጣን ቫልጣ ከጣርልኖርማ ቤት ከወጡ በኋላ ባስክና በረኛው ማሪዩን አንስተው ከነበረበት ትንሹ ክፍል ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል አስገቡት ። ሐኪሙ ብዙም ሳይቆይ መጣ ። የመንገድ አልጋም እንዲዘረጋ አዘዘና ማሪዩን ከዚያ ላይ አስተኙት ይመረምረው ገባ ።

የማሪዩ ውስጣዊ አካል አልተጎዳም ። የመታው ጥይት የጐን አጥን ቱን ከላይ በጨረፍታ ነካው እንጂ ዘልቆ አልገባም ። ከአንጉቱ ሥር ያለውና የተሰበረው አጥንት ግን በክርስ ምድሩ ጉዞ ምክንያት ከቦታው ተፈናቅሎ ወጥቶ ነበር ። ይህ ቁስል የሚያሳስብ ነበር ።

የማሪዩ ክንዶች በስለት ተሸረካክተዋል ። ጭንቅላቱም በስለት ተቆ ርጧል ። ፊቱ ግን አልተነካም ። እንሰሉ ይነካ አይነካ አልተረጋገጠም ። ከወገቡ በታች ያለው ክፍል አካሉ ግን መሉ በሙሉ ደህና ነበር ።

ሐኪሙ የማሪዩን ቁስሎች መርምሮ የጉዳቱን መጠን ከተረዳ በኋላ ፊቱንና ጸጉሩን በቀዝቃዛ ውሃ አጠበለት ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማድማዜል ዠልኖርማ መንፈሷ ተረበሸ ከወዲያ ወዲህ ከወዲህ ወዲያ ስትራወጥ ነበረች ፣ «ወይ እግዚአብሔር! እንዴት ሊሆን ቻለ!» እያለች ። አባቷም ጫጫታ ሰምቶ ከመኝታው ተነስቶ ወደ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ቀስ ብሎ ገባ ። ዠልኖርማ በከተማው ውስጥ በተ ነሳው አመጽ ምክንያት በጣም ተበሳጭቶ ፣ ተቆጥቶም ነበር ። ባለፈው ሌሊት ሳይተኛ አድሯል ። ቀኑም መሉ ትኩሳት ይዞት ዋለ ። ሲመሽም

@OLDBOOKSPDF

በጊዜ ወደ መኝታው ሐዶ ነበር ። አሁን ግን ጫጫታው አላስተኛ ብሎት ነው ተነስቶ የመጣው ።

ገርልኖርማ የማሪዩን ሁኔታ ሲያይ በጣም ተደናገጠ ። በጣምም ተረበሸ ። «ማሪዩ!» ሲል ጮኸ ።

«አሁን ነው ይዘውት የመጡት ጌታዩ..... ከምሽጉ ቦታ ነበረ አሉ» አለው ባስክ ።

«ሞቷል?» ሲል ጠየቀ ቀጠል አደርጎ ፤ «ሞቷል ወይንስ በሕይወት አለ ዶክተር?»

ሐኪሙ መልስ አልሰጠውም ። እሱም ራሱ በማሪዩ ሁኔታ ተረብሾ ነበር ።

«ሞቷል! ሞቷል! ሞቷል!» ሲል ጮኸ ገርልኖርማ ፤ «እስቲ ማን ሐኪ አለው! ብቻ ለምን እንደሐዲ ገብቶኛል! እኔን ጠልቶ ነው የሐዲው ። ደም የጠማው ልጅ! እና ሐዶ ተገደለ!»

ወዲ መስኮቱ ሐዶ ሙሉ በሙሉ ከፈተውና ያነበንብ ጀመር ፤ «እኩይ! ይመለሳል ብዬ እንደምጠብቀው እያወቀ.....! ክፍሉ ተዘጋጅቶለት.....! የልጅነት ምስሉ ከአልጋው ራስጌ ተደርጎለት.....! በፈለገበት ጊዜ ቢመጣ እቅፌ እንደምቀበለው እያወቀ.....! እኩይ.....! እኔን ለመበቀል ብሎ ነው ከምሽጉ ሐዶ የተገደለው.....! ለምን? የንጉሣዊ አገዛዝ ስለምደግፍ!»

ዶክተሩ ወዲ ገርልኖርማ ሐዶ እጁን ያዝ አደረገው ፥ ሊያረጋጋው አስቦ ። ገርልኖርማ ግን ሊረጋጋ አልቻለም ። ቀጠለ ማነብነቡን ፤ «አዬ ማሪዩ! ተገደልህ? ተቀጨህ? ሬሳህን ይዘውልኝ መጡ?» አለና ዓይኑን ወደ ሐኪሙ መልሶ ፤ «ዶክተር..... የተቆጣህ አይምስልህ! » አለው ፤ «የሞተን ሰው መቆጣት ምን ዋጋ አለው? ይህንን ልጅ ያሳደግሁት እኔ ነኝ ። እሱ ሲወለድ እኔ ሽማግሌ ነበርኩ ። አንድ ቀን ትንሽ ተጨቃጨቅንና ‘ሉዊ 18ኛ ይውደም’ ብሎ ወጥቶ ሐዶ ። ጥሩቱ የኔ አልነበረም ። እና እናቱ ሞታለች ። አባቱ ወንበዴ ነበር ። ይሁን እንጂ ልጅ በአባቱ ጥፋት አይወቀስም። በልጅነቱ በጣም የሚወዱድ ልጅ ነበር ። ቆንጆም ነበር ። እኔ ነኝ ያሳደግሁት ። እና አሁን ሞተ! ገድለውት ሬሳውን አመጡልኝ!»

ገርልኖርማ ወዲ ማሪዩ ተመልሶ የብቻ ንግግሩን ቀጠለ ፤ «ጨካኝ.....! ጫካኝ ልጅ.....! ከአሁን ወዲያ ግድ የለኝም ። የእኔም ቀን ተቃርቧል ። ሞቼ አርፈዋለሁ ። ይብላኝ እንጂ ለሱ! ከልጃገረዶች ጋር በመቦረቅ ፈንታ መዋጋቱን መረጠ ። እና ተገደለ! ግን ለምን ብሎ? ለሬፑብሊክ? የተረገመ ሬፑብሊክ! የሱ ሞት የኔንም ሞት ያፋጥነዋል ። ይሁን ግድ የለም ። ይኸው ይሻለኛል ። በጣም አርጅቻለሁና ሞቼ ባርፈው ይሻለኛል ። እስከ ዛሬም በሕይወት መቆየት ባልተገባኝ ነበር ። የተረገመ ዘመን!»

@OLDBOOKSPDF

እንዲሁ በብስጭትና በጸጸት ሲያነበንብ ሳለ ማሪዩ ዓይኖቹን ቀስ ብሎ ገለጣቸው ። ዓይኖቹ በጊልኖርማ ዓይኖች ላይ አረፉ ። ጊልኖርማ በሕልም ውስጥ ያለ መሰለው ። «ማሪዩ!» ሲል ጮኸ ፤ የደስታ ጩኸት ፤ «ማሪዩ! ሕጻኑ ልጄ ማሪዩ! በሕይወት አለህ!» ብሎ ጮኸና ወዲያውኑ ሕሊናውን ስቶ ወደቀ ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሦስት

ያዳለጠው ጣቪር

— 1 —

ጣቪር እንጉቱን ደፍቶ እጆቹን ከበስተኋላው አነባብሮ ከሎም አርሚ ጐዳና ተንሰቶ ዝቅዝቅ ወደ ሴት መንገ አቅጣጫ አመራ ። በሕይወቱ ውስጥ እንገቱን ደፍቶ እጆቹን ከበስተኋላው አነባብሮ ሲራመድ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ። በተለምዶ እንደ ናፖሌዎን ደናፓርት በልበ—ሙሉት ከንዶቹን ደረቱ ላይ አጣምሯቸው ራሱን አቅንቶ ይዓዝ ነበር ።

ሐዶ ሐዶ ከሴት መንገ ሲዳርስ እደገኛ ከሆነ ሥፍራ ላይ ቆመ ። ይህ ሥፍራ መንዙ ቦታይል የሚወረወርበት ማዕበልም የሚበዛለት ሥፍራ ነው ። አንዱ አጋጣሚ ሆኖ ከዚያ ሥፍራ አዳልጦት ውሃው ውስጥ የገባ ሰው ዋናተኛ ቢሆን እንኳ ተመልሶ የመውጣት ዕድል የለውም ። እጅግ በጣም አደገኛ ሥፍራ ነው ። ከዳርቻው ለምችን ከአዲጋ ለመጠበቅ ታስቦ የተሠራ አጥር መሳይ መከላከያ አለ ። ጣቪር መከላከያውን ደገፍ ብሎ ያሰላስል ፣ ሕሊናውን ይመረምር ገባ ።

ሁለት የማይጣጣሙ ሃሳቦች በአእምሮው ውስጥ ተነሱበት ። አንደኛ ፣ ውለታ መላሽነት ፣ ሁለተኛ ፣ ግዳጅ ፈጻሚነት ። በአንድ በኩል ጓጉን ቫልጣ ሕይወቴን ስላዳነልኝ ውለታ መላሽ መሆን ይገባኛል.... እሱን ይገደ ሕግ ፊት ማቅረብ አይቻለኝም» አደለ ሲያስብ በሴላ በኩል ደሞ ፣ ጓሱን ነጻ ለቅቂ ውለታ መላሽ ብሆን ሕጋዊ ግዳጇን መርሳት ይሆንብኛል» አደለ ያስባል ። ሁለቱ ተጻራሪ ሃሳቦች በአእምሮው ውስጥ ይፋለሙ በታል ።

ግዳጅ ይበልጣል ብሎ ወደ ሎም አርሚ ጐዳና ተመልሶ ጣን ቫልጣን ይዞ ለማሠር በሚያስብበት ጊዜ ሁሉ አንዳች ውስጣዊ ኃይል ያግደዋል ። ይህ ውስጣዊ ኃይል ምን እንደሆነ ፈጽሞ አልገባህ አለው ።

@OLDBOOKSPDF

ሁለቱ ተፋላሚ ሃሳቦች አልሸናነፍ አሉት ። «እንዴት ነጻ አሰቀዋለሁ? አሱን ብቻ ሳይሆን ተሸክሞት የመጣውን አመጸኛ እንዴት አሰቀዋለሁ? የመንግሥት ኃይሬ እየበላው ማዳጀን ሳልፈጽም እንዴት እቀራለሁ?» እያለ ያስባል ። «ግን ይህንን ሰውዬ እንዲት አድርጌ ሕግ ፊት አቀርበዋ ለሁ? ሊበቀለኝ ሲችል አልተበቀለኝም ። ሊጠላኝ ሲችል አልጠላኝም» ሲልም ያስባል ።

ግቨር በመለወጥ ላይ ነበር ። በመለወጥ ላይ መሆኑንም ሳይረዳው አልቀረም ። ቀደም ብሎ ከሕግ ልዕልና ውጭ ሌላ ምንም ነገር ያለ አይመ ስለውም ነበር ። አሁን ግን ሞራል—ነክ የሆኑ ነገሮች ለምሳሌ ፥ ርኅራሄ ይቅር ባይነትና ደግነት እንዳሉ ተገነዘበ ።

«ሊገድለኝ ሲችል ለምንድነው ሳይገድለኝ የቀረው? በግዳጅ ምክን ያት አይደለም ። በግዳጅ ምክንያት ካልሆነ ለምንድነው የማረኝ? እኔሳ ብሆን እቤቱ አድርሼው ትቼው መምጣቴ በምን ምክንያት ነው? በግዳጅ ምክንያት? አይደለም ። ሌላ ምክንያት አለው ። ከግዳጅ በላይ የሆነ ሌላ ኃይል አለ ማለት ነው» ሲል አሰላሰለ ግቨር ።

ይህ ኃይል እግዚአብሔር መሆኑን ተገነዘበ ። ግንዛቤውም የቀድሞ እምነቱን አናጋበት ። በቀድሞ ጊዜ የመጨረሻው ኃይል የሰው ሕግ መስሎ ይታየው ነበር ። ይህንን ሕግ ሲያገለግልም ነው የኖረው ። አሁን ግን ከሰው ሕግ በላይ ሌላ ኃይል መኖሩን ሲረዳ የቀድሞ ሕይወቱ ትርጉም አልባ ሆነ በት ። ለመኖርም በቂ ምክንያት አጣ ።

ግቨር ያለበትን ቦታ ለቅቆ አንገቱን አቅንቶ ወደ አንድ ፖሊስ ጣቢያ አመራ ። ከዚያ ሲደርስ አንድ የአምላ አለቃ መኖሩን በመስኮት አየ ። የአምላ አለቃው ካለበት ክፍል ገብቶ ማንነቱን ተናግሮ ቁጭ አለ ። ከአጠ ገቡ ባለ ጠረጴዛ ላይ የበራ ሻማ ፥ መጻፊያ ብዕር ፥ የቀለም ብልቃጥ ፥ እና ወረቀቶች አዩበት ።

ግቨር ብዕሩን አንስቶ ወረቀቱን አቅርቦ ቀጥሎ ያለውን ይጽፍ ጀመር ።

<u>ለፖሊስ አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች ፤</u>

1ኛ፤ ከሁሉም በፊት የፖሊስ አዛዡ እነዚህን ነጥቦች እንዲመለከቷ ቸው እለምናለሁ ።

2ኛ፤ አስረኞች ተመርምረው ሲወጡ ፍተሻ በሚደረግላቸው ጊዜ ባዶ እግራቸውን ንጣፍ ድንጋይ ላይ እንዲቆሙ ይደረጋል ። ብዙዎቹ ወደ ወህኒ ቤት በሚመለሱበት ወቅት ያስላቸዋል ። በዚህ ሰበብ የሕክምና ወጪ ከፍ ይላል ።

@OLDBOOKSPDF

3ኛ፤ በፖሊሶች የሚያረገው የትብብሎሽ ክትትል መልካም አሠራር ነው ። ነገር ግን የዚህ ዓይነት ክትትል በሚያረግበት ጊዜ ክትትሉን የሚያደርጉት ቢያንስ ሁለት ፖሊሶች መሆን ይገባቸዋል ። ይኸውም አንደኛው ፖሊስ በምንም ምክንያት ደከም ብሎ ቢገኝ ሁለተኛው እንዲቆጣጠረውና እንዲተካው ነው ።

4ኛ፤ የማድሎኦት ወህኒ ቤት ልዩ ደንብ አገድ እስረኛ ግንዘብ ከፍሎ እንኳ በወንበር እንዳይቀመጥ ይከለክላል ። ይህ ደንብ ትርጉም የለሽ ነው ።

5ኛ፤ በማድሎኔን ወህኒ ቤት ባሉት የመዝናኛ ክፍሎች በኢያንዳንዳቸው ሁለት ባንኪኒዎች ብቻ ስላሉ አሳላፊዎ እስረኞቹን በእጅጥ እንዳትነ ካቸው የሚያግዳት ነገር የለም ።

6ኛ ስም ጠሪዎች የእስረኞችን ስም በግልጽ ለመጥራት እስረኞቹን ሁለት ሁለት ሉ ያስከፍሏቸዋል ። ይህ ክፍያ ስርቆት ነው ።

7ኛ፤ በፈትል ሱቅ ለተበጠሰ ክር ማካካሻ በሚል ሰበብ ኮንትራክተሩ ከእስረኞቹ አስር ሱ በመያዣ መልክ ይወስድባቸዋል ። ይህ መያዣ ኮንትራክተሩ ያለአግባብ የሚያስከፍለው ሂሳብ ነው ፤ አንድ ክር ቢበጠስ በመሠራት ላይ ያለው ጨርቅ አይበላሽምና ።

8ኛ/ የላፎርስን ወህኒ ቤት የሚጐበኙ እንግዶች ወደ ሴንት—ሚሪ ሊጂፕሲየን እንግዳ ማረፊያ ክፍል ለመድረስ በጣልጀት ሚዳይ ማለፍ አለባቸው ። ይህም እንግዶችን ቅር የሚያሰኝ ነው ።

9ኛ፤ ዳኞች እስረኞችን በሚመረምሩበት ጊዜ ፖሊሶች ይገኛሉ ። ፖሊሶች የሰሙትን ለሌሎች ሰዎች ሲያወሩላቸው ይሰማል ። ፖሊሶች ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ ስላለባቸው ፤ የዚህ ዓይነት ወሬኛነት ትክክለኛ ድርጊት አይደለም ።

10፤ ማዳም አንሪ ትክክለኛ ሴት ነች ። በጎ ቢቷም ንጹህ ነው ። ይሁን እንጂ ወደ ምስጢራዊው መታሠርያ ቦታ የሚወስደውን መተላለፊያ በሴት እንዲጠበቅ መደረጉ ትክክል አይደለም ።

«አንደኛ ደረጃ ተቆጣጣሪው» የሚል ጽሑፍ አሠፈረበትና ሰሙን ፈረመበት ግሪፎር ።

«የሻትሌ አደባባይ ፖሊስ ጣቢያ

ስኔ ሰባት ቀን 1832 ዓ.ም. በግምት ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት» የሚል ጽሑፍም አሰፈረበት ።

@OLDBOOKSPDF

ግቪር ቀለመን አድርቆ ወረቀቱን አጣጠፈውና አሸገው ። ፈለአስተ ዳደሩ የተጻፈ ማስታወሻ» የሚል ጽሑፍም በጀርባው አሰፈረበት ። ከዚያ በኋላ ደብዳቤውን ጠረጴዛው ላይ ትቶት ወጥቶ እንደገና ወደ ሴን ወንዝ አመራና ከዚያ ሲደርስ ቀደም ብሎ ቆሞበት በነበረ አደገኛ ሥፍራ ላይ ቆመ ።

ፍጹም ጭለማ ሆነ ። የሰማይ ከዋክብት በደመና ተሸፍነዋል ። የሚያልፍ ሰው አይታይም ። መንገዶች በሙሉ ርጭ ብለዋል ። ግቪር የቆመበት ቦታ ግን በመንገድ መብራት ብርሃን ይታያል ።

ሰሞኑ በጣለው ዝናብ ምክንያት የሴን ወንዝ ሞልቷል ። ውሃው እንደዘንግ ይወረወራል ። አዝዋሪትም አለበት ።

ግቪር ጐንበስ ብሎ ወንዙን ተመለከተው ። የጭለማ ገደል መስሎ ታየው ። ውሃው ባይታየውም እንኳ ጉርምርምታው ይሰማዋል ።

ግቪር ባርኔጣውን አውልቆ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ከዚያም በኋላ ዘልሎ ከጭለማው ገደል ውስጥ ገባ ። ውሃው ተንቦራጨቀ ። ግቪር ወረደ..... እየሰጠመ..... እየሰጠመ ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አራት

የልጅ ልጅና አያት

— 1 —

ማሪዩ አራት ወር ሙሉ በስቃይ ከቀየ በኋላ ከሞት መትረፉን ሐኪሙ አረጋገጠ ። ሆኖም ሲተጨማሪ ሁለት ወራት ከመኝታው ለመነሣ ሳት ሳይችል ቀረ ።

ታምሞ በቆየባቸው ስድስት ወራት ውስጥ ከፖሊሶች ዓይን ተግልሎ በመቆየቱ የሚከታተለው ሰው አልነበረም ። በእርግጥ የፓሪስ ፖሊስ አዛዥ ፣ ገርስኪ ፣ ዶክተሮች በአመጹ ምክንያት ቆስለው የሚያክሟቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር አንዲያቀርቡ አዝዞ ነበር ። ነገር ግን ይህ ትዕዛዝ የባሰውን የሕዝብ ቁጣ አስከተለ ። በዚህ ምክንያት በወጊያው ጊዜ እጅ ከጥንጅ ከተያዙት አመጸኞች በስተቀር ሌሎች ቁስለኞች ፣ ማሪዩ ጭምር ከክትትል ነጻ ሆኑ ።

ዣልኖርማ በየቀኑ ማታ ማታ ማሪዩ ከተኛበት ሐዲ ይጠይቀዋል ። ሁኔታውን ይከታተላል ። የቁስሉ ፋሻ ሲቀየርለት ይመለከታል ። ማሪዩ ከሞት መትረፉን ዶክተሩ ያረጋገጠለት ዕለትም እጅግ በጣም ደስ አለው ።

ማሪዩ ይበልጥ እየተሻለው በሐዲ ቁጥር ዣልኖርማ በዚያው ልክ ደስ ደስ እያለው ሐዲ ። «አውነት እስጊው ሁኔታ አለፈ» እያለ ዶክተሩን አሁንም አሁንም ይጠይቀዋል ። በጣም ቢያረጅም ከደስታው ብዛት የተነሳ ሰውነቱ ግርማ ሞገስ እየተጐናጸፈ ሐዲ ።

ማሪዩ ግን እየተሻለው በሐዲ ቁጥር ስለኮዜት እንጂ ስለሌላ ነገር አያልምም ነበር ። ምን እንደደረሰበት አያውቅም ። በሻንቬሪሪ ገዳና የተደረገውም ወጊያ እንዴ ጉም ሆኖ ይታየው ጀመር ። ኤፖኒን..... ጋቭሮሽ..... ቱናርድዬ..... ኤንጮልራ ሌሎቹ ጋደኞቹ..... እነዚህ ሁሉ እንደጉም

@OLDBOOKSPDF

ሆነው ይታዩታል ። ከወደቀበት ግን እንዳነሳው ፣ ወደቤቱ ግን እንዳመጣው አያውቅም ። የሚነግረውም ሰው አላገኘም ።

እየተሻሰው በሐዲ ቁጥር ኮዜትን ፈልጎ ለማግኘት ቁርጥ ሀሳብ አደረገ ፣ ሕይወቱን ከኮዜት ሕይወት ለይቶ ለማየት አይችልም ነበርና ።

የአያቱ መንሰፍሰፍ ግን ሊያሰልሰው አልቻለም ። አያቱ በአባቱ ላይ የፈጸመውን ግፍ ሊረሳው አልቻለም ። ኮዜትን እንዳያገባት መክልከሉም አልዋጥልህ አለው ። «እንዳገባት ካልፈቀዱልኝ በስተቀር እንዲያውም ቁስሌን አባብሰዋለሁ ። ምግብም አልቀምስም እላለሁ» እያለ ያስብ ጀመር ።

አንድ ቀን ጊልኖርማ ማሪዩ ከተኛበት ክፍል መጥቶ ፤ «እይ የኔ ልጅ..... እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ከአሳ ይልቅ ሥጋ በመረጥሁ ነበር ። ለሚያ ግማም ሰው ከሥጋ የተሻለ ምግብ የለም» አለው ።

ማሪዩ ከተኛበት ቀና ብሎ እጆቹን አንሶላው ላይ አኑሮ አያቱን አተኩሮ እያየ ፤ «አንድ የምነግርህ አለኝ» አለው ።

«ምንድነው አሱ?» ሲል ጠየቀው ጊልኖርማ ።
«ትዳር ለመያዝ እፈልጋለሁ ።»
«ጥሩ ነዋ!» ብሎ ይስቅ ጀመር ጊልኖርማ ።
«ጥሩ ነው?»
«አዎን ። የምታፈቅራትን ልጅ ልታገባት ትችላለህ ።»

ማሪዩ ጆሮውን ማመን አቃተው ።

«አዎን ልታገባት ትችላለህ» አሰው ጊልኖርማ ፤ «ስለልጅቷ አጠያይቄ ደርሼበታለሁ ። በሎም አርሜ ገዳና በቁጥር 7 ሕንጻ እንደምትኖር ሰምቻለሁ ። ልጅቷ ቆንጆ ነች ። ደሞም ጭምት ነች ። በጣም እንደምትወድህ ተረድቻለሁ ። አንተ ብትሞት ኖሮ እሷም እኔም በሕይወት ለመቆየት ባልቻልን ነበር» አለውና ፤ «አይስማማልኝም ብለህ ፈርተህ ነበር..... አይደለም እንዴ? ላገባ እፈልጋለሁ ስለው ይቆጣኛል ፣ ይናደዳል ብለህ አስበህ ነበር..... አይደለም እንዴ? እኔ ግን ከአሁን ወዲያ ፈጽሞ አልቃወምህም ። የምታፈቅራትን ልጅ እንድታገባት ፈቅጄልሃለሁ» አሰው ።

«አባባ!» አለው ማሪዩ በዚህ ጊዜ ።
«አ! ትወደኛለሃ!» አለው ጊልኖርማ ።

ሁለቱም የደስታ ሲቃ ይሟቸው ለአፍታ መናገር አልቻሉም ። ከዚያ በኋላ ግን ጊልኖርማ ፤ «ይገርማል! አፉ ተፈታ! አባባ ብሎ ጠራኝ!» አለ ።

«አባባ..... ጢናዬ ስለተሻለኝ ላያት እወዳለሁ ።»
«መልካም.....! ነገ ታያታለህ ።»

@OLDBOOKSPDF

«አባባ.....»
«ምንድነው አሰብ»
«ለምን ዛሬውኑ አላያትም»
«ከፈለግህ ዛሬውኑ አስጠርቼአት እንድትግናኙ አደርጋለሁ ።»

ከዚት ተጠርታ መጣች ።

«ድንቅ!» አለ ገርልኖርማ ገና ሲያያት ።

ከዚት ማሪዩን እቅፍ ብታደርገው ባልጠላች ነበር ። ነገር ግን በሰው ፊት እቅፍ አድርጋ ልትስመው አልደፈረችም ።

ከአባቷ ጋር አብረው ነው የመጡት ። ግን ቫልዣ ወይም እነሱ እን ደሚያውቁትና እንደሚጠሩት ፎሽለቫ ጥቁር ሙሉ ልብስ ለብሷል ። ነጭ ክራቫት አስሯል ። ልብሶቹ አዳዲስ ናቸው ። ወደቤት ያስገባው በረኛ ማሪ ዩን ተሸክሞ ያመጣው ዕለት ቢያየውም አላወቀውም ፤ ያን ቀን ያደፈ ልብስ ከመልበሱም በላይ ፊቱ በደም ተለውሶ ነበርና ።

ግን ቫልዣ ትልቅ መጽሐፍ የመሰለና በአረንጓዴ ወረቀት የተጠቀ ለለ ነገር ይዞ ነው የመጣው ።

መጽሐፍ የሚትወድዋ ማድሚዜል ገርልኖርማ ዓይኗን ወደ ኒኮሌት መልሳ «ይህ አዛውንት ሁል ጊዜም መጽሐፍ ተሸክሞ ይሆን እንዴ የሚዘ ረውን» ስትል ጠየቀቻት ። አባቷ ሰማትና ፤ «ታዲያ ምን አለበትና የተማረ ሰው ቢሆን ነው! አንድ የማውቀው ሰው እንዲሁ አሮጌ መጽሐፍ ከእጁ አይጠፋም ነበር» አላት ። ቀጠል አድርጎም ወደ ግን ቫልዣ አያየ ፤ «ሙሴ ትራንሽለቫ.....» አለው ። ገርልኖርማ «ሙሴ ፎሽለቫ» ስማለት ፈልጎ ነበር ። ነገር ግን የሰውን ስም በትክክል ማስታወስ ይቸግረው ነበር ።

«ሙሴ ትራንሽለቫ..... ልጅህን ለልጅ ልጄ ለባሮን ማሪዬ ፖሜርስ ስጠኝ ስልህ ክብር ይሰማኛል» አለው ።

«ሰጥቼሃለሁ» አለው ዣን ቫልዣ ።

ይህንን ቃል ከተለዋወጡ በኋላ ማሪዬና ከዚት ይጨዋወቱ ጀመር ። «ወይ አግዚአብሔር! እንደገና ተገናኘንም አይደል!» አለችው ከዚት ፤ «ለ መሆኑ ምን አሳብዶህ ነው ወደ ውጊያው ቦታ የሔድከው፣ ጨካኝ ነህ..... ምን ቢደልህህና ነው ወደዚያ የሔድከው፣ እንዴት ሰማቸልህ ነበር! ለማንኛውም ብቻ ያለፈው አልፏል ። ወደዚህ እንድመጣ ሲነግሩኝ እንዴት ደስ አለኝ መሰለህ! ተቻኩዬ ልብሴን እንኳ በቅጡ አልለበስኩም ። ሰው ምን ይለኝ ይሆን!»

«መልአክ ነው የምትመስይው» አላት ማሪዬ ።

@OLDBOOKSPDF

በዙሪያቸው ሰው መኖሩን ልብ ሲሉ አፍረው ዝም ዝም አሉ ። ቀስ ብለው ግን እጅ ለእጅ ተነካኩ ።

ገርልኖርማ ዓይኑን ወደ ኮዜት መልሶ «እንዴት ቆንጆ ነች! ታድለ ሃል ማሪዩ። እንደዚህ ባላረጅ ኖሮ እኔና አንተ በተጋደልንባት ነበር» ብሎ «በቅዱስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ትጋባላችሁ ። የቤተክርስቲያን ጋብቻ ይሻላችኋል ። ብዙ ተባ... ...ል መጽሐፉም» ብሎ «በነገራችን ላይ..... አንድ የልብ ጓደኛ አልነበረህም እንዴ?» ሲል ጠየቀው ።

«ነበረኝ..... ኩርፌራ.....» አለው ።
«ምን ሆነ ታድያ?»
«ተገድሏል ።»

ገርልኖርማ የማሪዩንና የኮዜትን አራት እጆች ሰብሰብ አድርጎ ይዞ «ኮዜት ውበ ነች ። ቅንድቦቿ ምንኛ ደስ ይላሉ!» አለ ።

ቀጠሶ ንግግሩን ፤ «ልጆቼ..... በትክክለኛው ጐዳና ላይ ነው ያላችሁት ። እርስ በርሳችሁ ተፈቃቀሩ» ብሎ ፤ «እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ የገንዘብ ችግር አይኖርባችሁም ። እኔ ከሞትሁ በኋላ ግን እንጃ!» አለ ።

«ማድሚዜል ዩፍሬዚ ፎሽለቫ ስድስት መቶ ሺ ፍራንክ አላት!» የሚል ድምጽ ሰሙ ልክ በዚህ ጊዜ ። የጣን ቫልጣ ድምጽ ነበር ።

«ማድሚዜል የፍሬዚ ደሞ ማን ናት?» ሲል ጠየቀው ገርልኖርማ ።

«እኔ ነኝ» አለችው ኮዜት ።
«እና ስድስት መቶ ሺ ፍራንክ?» አሰ ገርልኖርማ ።

«አስራ አምስት ወይም አስራ ስድስት ሺ ፍራንክ ቢጎድል ነው ። ስለዚህ ስድስት መቶ ሺ ቢባል ይቀላል» ብሎ ጣን ቫልጣ ይዞት የመጣውን ጥቅል ጠረጴዛ ላይ አኖረው ። ጥቅሉ ገንዘብ እንጂ መጽሐፍ አልነበረም ።

ጣን ቫልጣ ራሱ ጥቅሉን ከፈተው ። ውስጡ የወረቀት ገንዘብ ብቻ ነበር ። ቢቆጠር ልክ አምስት መቶ ሰማንያ አራት ሺ ፍራንክ ሆነ ።

ገርልኖርማና ሴተ ላጤዋ ልጁ በገንዘቡ ብዛት በጣም ተደነቁ ። ማሪዩና ኮዜት ግን የሚያስቡት ስለገንዘቡ ሳይሆን ስለፍቅራቸው ነበር ።

— 2 —

ጋርን ቫልጣ በሻማት የ ጐዳይ ራሱን አጋልጦ ፣ ወህኒ ቤት ገብቶ ፣ ከዚያም ለአጭር ጊዜ አምልጦ ወጥቶ በነበረበት ወቅት ወደ ፓሪስ ሔዶ ቀደም ብሎ ያፈራውን ሀብት ከላፊት ባንክ አውጥቶ እንደገና እያገ ይሆ ናል በሚል ፍራቻ ሀብቱን በሞንፈርመይ ጫካ ውስጥ በቱልል ድንጋይና

@OLDBOOKSPDF

ቆርቆሮ በተመታበት ዛፍ መሐከል ባለው ገላጣ ሥፍራ ጉድጓድ ምሶ ቀብሮት ነበር ። አቡነ ሚሪዬል የስጠጉንም መቅረዞች ከገንዘቡ ጋር ሳጥን ውስጥ አድርጎ ቀብሮአቸው ነበር ። የነበረው ጠቅላላ ሀብት ስድስት መቶ ሠላሳ ሺ ፍራንክ ነዮር ።

ዣን ቫልዣ ገንዘብ ባስፈለገው ቁጥር በሌሊት ወደ ሞንፈርመይ ሔዶ ጫካው ውስጥ ገብቶ ጉድጓዱን ምሶ ያስፈለገውን ያህል ቆንጥሮ ይወስድ ነበር ። በየጊዜው ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት ገብ እሔዳለሁ ብሎ ከቤቱ የሚወጣው ወደዚያ ለመሔድ ሲፈልግ ነበር ። ጉድጓድ የሚምስበትን ደማ ጫካው ውስጥ የሚደበቅበት ቦታ ነበረው ።

ማሪዩ ማገባም ሲጀምርም ዣንዘብ ያሚያስፈልገው ጊዜ መድረሱን በመገንዘብ ወደ ሞንፈርመይ ጫካ ሄዶ ያለውን ሀብት በሙሉ መቅረዞቹን ጭምር ቆፍሮ አውጥቶ ወደ ፓሪስ ይዞ መጣ ። የቀረው ጠቅላላ ገንዘብ አምስት መቶ ሰማንያ አራት ሺ ፍራንክ ነበር ። አምስት መቶ ፍራንክ ብቻ እነሳለትና ቀሪውን ሀብት ለእነኮዜት አስረከባቸው ። መቅረዞቹን ግን በመኖርያ ቤቱ ውስጥ በእሳት ማንደጃው ላይ በነበረው መደርደርያ ላይ አኖራቸው ።

ዣቨር ራሱን መማደሉን ከመስማቱም በላይ «ሞኒተርን» በተባለው ጋዜጣ ተጽፎ አይቶ ስለነበረ ከክትትል ነጻ መሆኑን ተረዳ ዣን ቫልዣ ። ዣቨር ጽፎ ያስቀረው ማስታወሻ ሲመረመር ጭንቅላቱ ትክክል አይሠራም ከሚል ግምት አድርሶ ነበር ። ዣን ቫልዣም ፤ ዣቨር ነጻ የለቀቀኝ በእርግጥም አእምሮው ቢሰናከልበት ነው፡፡ ሲል አመነ ።

— 3 —

ማሪዩ በሆነው ሁሉ ቢደሰትም መልስ ያላገኘላቸው ሁለት ጥያቄዎች አእምሮውን ይቆረቁሩት ነበር ። የአባቱ ባለ ውለታ የነበረው ቴናርዲዬ ከምን ደረሰ? እሱንስ ያዳነው ሰውዬ ማን ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ቆረጠ ማሪዩ ።

ሲጠይቅ ሲያስጠይቅ ከሰነበተ በኋላ የቴናርዲዬ ሚስት እስር ቤት ውስጥ መሞቷን ፣ ቴናርዲዬ ራሱ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ሰማ ። ይሁን እንጂ እሱና ልጁ አዜልማ ከምን ጥጻሜ እንደደረሱ ለማወቅ ሳይችል ቀረ ።

ማሪዩ በሰው አማካኝነት ከሞት ስላዳነው ሰውዬ ማንነት መጠነኛ የሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ቻለ ። የወሬው ምንጭ ጋሪ ነጂው ነበር ። ጋሪ ነጂው በስኔ 6 ቀን የፖሊስ ወኪሉን ሲጠባበቅ እንደዋለ ፣ ከምሽቱ ሦስት

@OLDBOOKSPDF

ሰዓት ገደማ አንድ ሰውዬ በድን የመሰለ ሌላ ሰውዬን ተሸክሞ ከፓሪስ ከርሰ ምድር እንደወጣ ፣ በፖሊሱ ትዕዛዝ ጋሪ ነጂው ሰዎቹን በጋሪው አሳፍሮ ወደ ፌይ—ዱ—ካልቬር ጐዳና እንደወሰዳቸው ፣ ከዚያ በኋላ ፖሊሱንና ሰውዬውን ይዞ መጓዙና ከአንድ ቦታ ሲደርሱ እንዳወረዳቸው ፣ የማንጓጐጥ ሂሳቡን ተቀብሎ እንደሔደና ከዚያ ወዲያ ፖሊሱንና ሰውዬውን እንዳላያቸው ገለጸ ።

ማሪዩ ከዚህ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ሳይችል ቀረ ። በአደጋው ዕለት ባስክና ኒኮሌት በማሪዩ ሁኔታ መገረሳቸው በጣም ተረብሾ ስለነበረ ማሪዩን ያዳነው ሰው አስተውሰው አላዩትም ። በረኛውም ፤ «ሰውዬው ያስፈራ ነበር!» ከማለት በስተቀር ማንነቱን አብራርቶ ለመግለጽ ሳይችል ቀረ ።

በደም ተለውሶ የነበረው የማሪዩ ልብስ ሳይታጠብ እንዳለ እንዲቆይ ተደርጎ ነበር ። ይኸውም ስለለውዬው ማንነት ክትትል በሚደረግበት ወቅት ምናልባት አንዳች ፍንጭ ይሰጣል በሚል ተስፋ ነቦር ። ከኮቱ ቁራጭ ጨርቅ ተቀድዶ መውጣቱም ሌላ ፍንጭ ይሰጥ ይሆናል የሚል ግምት ሳይሰጠር አልቀረም ።

አንድ ቀን ማሪዩ ከሞት ያዳነውን ሰውዬ ለማግኘት ምን ያህል ጥረት እንዳደረገና ጥረቱ ግን ከንቱ ሆኖ መቅረቱን ለኮዜትና ለጣን ቫልጣ ገለጸ ላቸውና ፤ «ሰውዬው ማንም ይሁን ማንም አጅግ በጣም ደግ ሰው መሆን አለበት » አላቸው ፤ «የጥይት ናዳ እየወረደበት እኔን ተሸክሞ ከውጊያው ቦታ ማውጣቱ ፣ በከርሰ ምድር በጭለማ መንገዱ ፣ ለኔ ብሎ ሕይወቱን አደጋ ላይ መጣሉ ፣ ይህ ሁሉ ከማንም ተራ ሰው የሚጠበቅ አይደለም!» አለና ፤ «የኮዜት ሀብት የኔ ቢሆን ኖሮ ግን.....!» አለ ።

«ቢሆን ኖሮ ምን ታደርግ ኖሯል?» አለው ጣን ቫልጣ ።
«ሰውዬውን ፈልጎ ላገኘልኝ ሰው ሀብቴን በሙሉ እሰጠው ነበር ።»

«የኮዜት ሀብት ያንተም ሀብት ነው» አለውና ዝም አለ ጣን ቫልጣ ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አምስት

ሠ ር ግ

— 1 —

ከዜትና ማሪዩ ሲያልሙት የነበረው የሠርጋቸው ቀን ደረሰላቸው ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ የሠርጋቸው ዕለት ፥ የካቲት 16 ቀን «ካርናቫል» የተባለ የሕዝብ በዓልም ነበር ። የከተማው መንገዶች በሕዝብ ተሞልተዋል ። ሕዝቡ ይዘፍናል ። ይጨፍራል ። ከሕዝቡ መሐከል የፊት መሸፈኛ «ማስክ» ያደረጉ ወንዶችም ሴቶችም አሉባቸው ።

ሙሽሮቹና ቤተዘመዶቻቸው ከፊይ—ዱ—ካልቬር ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ለመሔድ ሠረገላቸው ላይ ወጥተው ጉዞ ጀመሩ ። ሙሽራውና ሙሽሪት ሥርዓተ ጋብቻቸው ከመፈጸሙ በፊት በአንድ ሠረገላ አንዳይጓዙ የዘመኑ ልማድ ይከለክላቸው ነበር ። ስለሆነም ከዜትና ማሪዩ በተለያዩ ሠረገላዎች ላይ ነበሩ ። በአንደኛው ሠረገላ ውስጥ ከዜት ፥ ማድሚዜል ገርልኖርማን ፥ ሙሴ ገርልኖርማና ጥጉ ቫልጣ ነበሩበት ። ጥጉ ቫልገር በሆነ ምክንያት እጁ በፋሻ ታስሯል ። ከንዱም በማንገቻ ተይዟል ።

በሁለተኛው ሠረገላ ማሪዩና አጃቢዎቹ ሲጓዝበት ነበሩ ።

በመንገድ ያለው ሕዝብ ስፍር ቁጥር ስለሌለው ሠረገላዎቹ እንደልባቸው ስመንቀሳቀስ አልቻሉም ። ሕዝቡ ይጨፍራል..... ይዘፍናል ። ሁካታው.....ጫጫታው..... ሬንጠዚያው ተሟሙሏል ።

ሬታቸውን በፊት መሸፈኛ «ማስክ» ከጋረዱ ሰዎች መሐከል አንድ አዛውንትና አንዲት ልጃገረድ ነበሩበት ። እንደሌላው ሰው ሁሉ እነሱም በማለፍ ላይ ያሉትን ሙሽሮችና አጃቢዎቻቸውን ሲመለከቱ ነበሩ ።

«ሰማሽ.....!» አለ አዛውንቱ ።

@OLDBOOKSPDF

«ምን አልክ አባዬ!» አለችው ልጅቱ ።

«ያንን ሽማግሌ ሰውዬ ኦየሽው!»
«የቱን?»
«በመጀመሪያው ሠረገላ ላይ ያለው ።»
«ከጎዴን በማንጋቻ የያዘው ?»
«አዎን ።»
«ታዲያ ለአንተ ምንህ ነው?»
«እርግጠኛ ነኝ አውቀዋለሁ ።» አለና ፤ «ሙሽሪቷ ትታይሻለች ለመ ሆኑ?» አላት ።
«አትታየኝም ።»
«ሙሽራውስ?»
«በመጀመሪያው ሠረገላ የለም ።»
«እሰቲ ሙሽሪቷን ልታያት ሞክሪ ።»
«አትታየኝም ።»
«ለማንኛውም እኛ በፋሻ የታሠረውና ከጎዴ በማንጋቻ የተያዘውን ሰውዬ አውቀዋለሁ» አላት ።
«ብታውቀው ምን ያደርግልሃል አባዬ?»
«ምን ይታወቃል ብለሽ.....!» አላትና ፤ «ከሠርጎኞቹ መሐከል ሊገኝ እንዴት ቻለ!» አለ ።
«እኛስ ብንሆን እዚህ ከሕዝቡ መሐከል ተገኝተን የለምን!»
«ሠርጎኞቹ ከወዴት ይሆን የመጡት?»
«እኔ ምን አውቄ!»
«ስሚ.....» አላት አዛውንቱ
«ምን?» አለችው ሴት ልጁ ።
«አንድ ነገር ማድረግ አለብን ።»
«ምን?»

«ሠርጎኞቹ እነማን እንደሆኑና ወዴትስ እንደሚሄዱ ማወቅ አለብን ። እሰቲ ተከታትለሽ ድረሽባቸው..... በልጅ እግርሽ» አላት ።

«ልከታተላቸው አልችልም..... ፖሊሶች ካዩኝ ይይዙኛል ።»

«እሱስ እውነትሽን ነው.....» አለና ፤ «ብቻ ያ ሽማግሌ በመጀመሪያው ሠረገላ ከተገኘ የሙሽሪት አባት መሆን አለበት» አላት ።

«በሆን ባይሆን ለአንተ ምንህ ነው?»

«ስሚኝ አዜልማ.....» አላት አዛውንቱ ሰውዬ ፤ «ዛሬ የፌት መሸፈኛ ማስክ ሊደረግ የሚቻልበት ቀን ስለሆነ ፊቴን ጋርጄ መጣሁ ። ነገ ግን የፊት መሸፈኛ ማስክ ሊደረግ ስለማይፈቀድ ወዴ ከርሰ ምድር ተመልሼ መደበቅ አለብኝ ። እንቺን ግን የሚያስፈራሽ ነገር አይኖርም ። እና ሠርግ ጭንብ ተከታትለሽ የት እንደሚሔዱ አረጋግጪልኝ» አላት ።

@OLDBOOKSPDF

— 2 —

ሙሽሮቹ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ከዜት ነጭ ቀሚስ ለብሳለች ። ቫል አድርጋለች ። ከሉል የተሠራ የአንገት ጌጥ አንጠልጥላለች ። እቅፍ አበባ ይዛለች ። እንደጸሐይ ታንጸባርቃለች ።

ማሪዩ ጥቁር ልብስ ለብሷል ። ጸጉሩ ያብረቀርቃል ። ሽቶ ተርከፍክ ፏል ። በግምባሩ ላይ ጠባሳ ይታይበታል ፤ በሻንቭረሪ ጐዳና በሰለት ተመ ትቶ ነበርና ።

ከቤተክርስቲያኑ ደርሰው ሥርዓተ ጋብቻው ተጀመረ ። የቀለበት ልውውጥ ተደረገ ። ከዜት ከደስታዋ ብዛት የተነሳ በሕልም ዓለም ትሁን በውን ዓለም ለይታ ለማወቅ ቸገራት ።

ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሞ ከቤተክርስቲያኑ ወጥተው ሠረገላቸው ላይ ወጡ ። በመልሱ ጉዞ ማሪዩና ከዜት በአንድ ሠረገላ ተቀመጡ ። ገርልኖር ማና ገኖን ቫልገ ከእነሱ ትይዩ ያለውን መቀመጫ ያዙ ። ማድሚዜል ገርል ኖርማ ግን ወደ ሁለተኛው ሠረገላ ተዛወረች ።

እቤት ሲደርሱ ለሠርጉ ተበለጠ ከተጌጠው የምግብ አዳራሽ ገቡ ። ሠርግ የተጠሩ በርካታ እንግዶችም ነበሩ ። ግብገኛው ተሚሚቀ ። መዚቃ ውም እንዲሁ ። ገኖን ቫልገ ግን እጇን እሞኛል ብሎ ግብገኛው ከመጀመሩ በፊት ተሰናብቶ ሔደ ። በባነጋው ተመልሶ እንደሚመጣ ግን አረጋገጠ ።

በግብገኛው ፍጻሜ ላይ ገርልኖርማ በጣም ረጅም ንግግር አደረገ ። መልእክቱ ግን አጭር ነበር ፤ «ተሳቀሩ.... ከፍቅር የበለጠ ነገር የለም» የሚል ።

ገርልኖርማ ንግግሩን ካበቃ በኋላ ማሪዩና ከዜት ወደ መኝታ ክፍላ ቸው አመሩ ።

— 3 —

ገኖን ቫልገ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ ሻማ አብርቶ ቢመለከት ቢ ቱ ባዶ ሆነበት ። ከዜት የለችም ። ቱሴም የለችም ። ቱሴ ከዜትን እንድታግለዓል አብራት ሔዳለች ።

ሦር ሦር ብሎ ቢመለከት ቁም ሳጥኖቹ በሙሉ ክፍት ናቸው ። ወደ ከዜት ክፍል አመራ ገኖን ቫልገ ። አልጋዋ ባዶ ነው ። አንሶላ እንኳ አል ተነጠፈበትም ። ብርድልብሶቹ ተጣጥፈው አልጋው ራስጌ ተደርገዋል ።

@OLDBOOKSPDF

ጐን ቫልገር ከክፍል ወደ ክፍል እየተዘዋወረ ቁም ሳጥኖቹንና በሮቹን ዘጋጋቸው ። ከዚያ በኋላ ሻማውን እንደያዘ ወደ ራሱ ክፍል ተመለሰ ። ዓይኖቹ ምን ጊዜም ከማይለየው ሻንጣው ላይ አረፉ ። ከአልጋው ራስጌ በአንድ ጠረጴዛ ላይ ነበር ።ሐድ ብሎ ከፈተው። ኮዜት ከሞንፈርመይ ስት ወጣ የለበሰቻቸው ልብሶች ጫማዎቿ ጭምር ከዚያ ውስጥ ነበሩ ። ስቦ አወጣቸው ጐን ቫልገር ። ከትውስት ዓለምም ውስጥ ገባ ። ኮዜት በቱናር ዲዬ ቤት ሳለች ትለብሳቸው የነበሩት ቡትዶ ልብሶች..... በፋንቲን ሞት ምክንያት እሱ ገዝቶ ያመጣቸው እነዚህ ጥቁር ልብሶች..... በልደት በዓል ዋዜማ ገዝቶ የሰጣት ትልቅ አሻንጉሊት..... በእንጨት ጫማዋ ውስጥ ያስ ቀመጠላት የወርቅ ፍራንክ..... እነዚህ ሁሉ ትዝ ሲሉት ዓይኖቹ እንባ ቋጠሩ ።

ጐን ቫልገር ከሕሊናው ጋር ይታገል ጀመር ። ከሕሊናው ጋር መታ ገል ሰሱ አዲስ ነገር አይደለም ። አቡነ ሚሪዬልን ካወቀ በኋላ ከሕሊናው ጋር ታግሏል ። ሻማትየ ተይዞ ከታሠረ በኋላ ከሕሊናው ጋር ታግሏል ። አሁንም ኮዜትና ማሪዩ ከተጋቡ በኋላ ከሕሊናው ጋር ይታገል ገባ ። ከአሁን ወዲያ በእነሱ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ሰመግባት ይችላል ወይ፣ ምን ማድረግ ይገባዋል? የሽምግልና ሕይወቱን በብቸኝነት ሊገፋው ነው ወይንስ ከእነሱ ጋር ይኖራል? ሌሊቱን ሙሉ ሲያስበና ሲያሰላስል አደረ ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ስድስት

የዣን ቫልዣ ኑዛዜ

— 1 —

በሠርጉ ማግሥት ስድስት ሰዓት ካለፈ በኋላ ወዶ ገርልኖርማ ቤት አመራ ዣን ቫልዣ ። ከእንግዳ መቀበያው ክፍል አጠገብ በነበረው አነስ ተኛ ክፍል ባስክን አገኘ ። ባስክ ክፍሉን ሲያጸዳ ነበር ። ሥራውን አቋርጦ ዣን ቫልዣን ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ይዞት ገባ ። «አርፍደን ነው የተነሳነው ጌታዬ» አለው ።

«ጌታህ ተንስቷል?» አለው ዣን ቫልዣ ።

«የትኛው? ትልቅዬው ወይንስ ትንሽዬዋ?»

«ትንሽዬው..... ሙሲ ማሪዩ ፓሚርሲ ።»

«አስቲ ሔጄ ልይልዎት»

«አኔ መሆኔን እንዳትነግረው ። ከመሻታው ከተነሳ በደረሳው ሰው ይፈልግሃል በለው ።»

ባስክ ማሪዩን ለመጥራት ሲሔድ ዣን ቫልዣ እንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ ብቻውን ቆየ ። በትናንቱ ሠርግ ምክንያት የክፍሉ ወለል በአበባ ርጋፊ ተዝረክርኳል ። በሻማ መቅረዞቹ የቀለጠ ሻማ ተከምሮባቸዋል ። መቀመጫዎቹ እዚህም እዚያም ተዝረክርከዋል ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ማሪዩ ገብቶ ፤ «አርስዎ ነዎት እንዴ አባባ ባስክ ሰው ይፈልግሃል ሲለኝ ሌላ ሰው መስሎኝ ነበር» አለው ፈገግ ብሎ ፤ «ትና ንትና ከግብግው በፊት በመሔድዎ ቅር ተሰኝቼ ነበር ። እጅዎን ተሻለዎት ለመሆኑ?»

@OLDBOOKSPDF

«አዎን ደህና ነኝ ።»

«ከዚትና እኔ ስለርስዎ ያላወራነው የለም ። የሚኖሩበት ክፍል ተዘጋጀ ቶሎታል ። ከአሁን ወዲያ በሎም አርሜ ጐዳና መኖር አያስፈልጎትም ። እዚሁ ከእኛው ጋር ቢኖሩ ይሻላል ። እንዲያውም ዛሬውኑ ጠቅልለው ቢመጡ ደስ ይለናል ። ደሞም አይስለችዎትም ። ከአያቴ ጋር ካርታ እየተጫወቱ ጊዜዎን በጥሩ ሁኔታ ያሳልፉታል ።»

«አመጣጤ ለሌላ ጉዳይ ነው» አለው ገን ቫልጉ ፤ «አንተ አታውቅም እንጂ እኔ የቀድሞ አስረኛ ነኝ ።»

ማሪዩ ደንገጥ አለ ።

ገን ቫልጉ ክንዱን ከማንገቻው አውጥቶ አውራ ጣቱ ላይ የጠመጠመውን ፋሻ ፈትቶ ለማሪዩ አሳየውና ፤ «ጣቴ ምንም አልሆነም» አለው ፤ «የቀድሞ እስረኛ በመሆኔ በጋብቻው ሕጋዊ ሰነድ ላይ የውሸት ስምና ፊርማ እንዳላሳርፍበትና ጋብቻው ሕጋዊነቱን እንዳያጣ በማሰብ ነው እጁን አሞኛል ብዬ ፋሻ የጠመጠምኩበት ።»

«ምን ማለትዎ እንደሆነ በትክክል የገባኝ አይመስለኝም» አለው ማሪዩ ።

«ሙሴ ማሪዩ..... ጽኑ እስራት ተፈርዶብኝ ወህኒ ቤት ውስጥ አስራ ዘጠኝ አመታት ኖሬአለሁ ። በስርቆት ወንጀል ነበር የተከሰስኩት ። ከዚያም በኋላ በሌላ ወንጀል ተከስሼ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶብኝ ነበር ። ነገር ግን አምልጬና ከሕግ ተሸሽጌ ነው የምኖረው ።»

ማሪዩ ይህንን ሲሰማ ዘገነነው ። ሰውነቱም ሽምቅቅ አለ ። «እሺ..... ይቀጥሉ» አለው ።

«ምናልባት አታምኑኝም ይሆናል ሙሴ ማሪዩ ። ነገር ግን እኔ የኮዜት አባት አይደለሁም ። ጥንት ዛፍ መልማይ ነበርኩ..... በፋቬሮል ። ገጠሬም ነበርኩ ። እውነተኛ ስሜም ገን ቫልጉ እንጂ ፎሽለቫ አይደለም ። ከኮዜት ጋር አንዳችም የሥጋ ዝምድና የለንም ። ስለዚህ በእኔ ምክንያት ጋብቻችሁ አንዳችም ሳንክ አይኖረውም ። ይህንን እንድታምኑኝ እፈልጋለሁ ።»

«እንዴት እርግጠኛ ለመሆን እችላለሁ ።»

«ሳልደብቅ እውነቱን ነው የነገርኩህ ።»

«እሺ አምኖታለሁ ።»

«ኮዜትን የሙት ልጅ ሆና ነው ያገኘኋት ። አባትም ሆነ እናት አልነበራትም ። ችግረኛ ልጅ ነበረች ። ማንም ሰው ቢሆን ለሕጻናት በተለይም

@OLDBOOKSPDF

ለተቸገሩ ሕጻናት ይራራል ። እኔም አራራሁላት ። ተንከባከብኳት ። ከእኔ ጋር እኑሬ አሳደግኋት ። አሁን ግን እሷና እኔ በተለያየ መንገድ ላይ ነው ያለነው ። እሷ ያንተ ሆናለች ። ደሞም ጥሩ ነው ። ያለኝን ሀብት አውርሻ ታለሁ ። ነገር ግን ይህ ሀብት ከወዴት መጣ ብለህ አትጠይቀኝ ። አስፈላጊ አይደለም ። በተረፈ ግን እውነተኛ ማንነቴን ማወቅ ይገባሃል በማለት ነው የነገርሁህ ።»

ማሪዩ የሚለውን አጥቶ ቆየና ፤ «ይህንን ለመናገር ማን አስገደድዎት? ምስጢርዎን ለራስዎ ሊያስቀሩት ይችሉ ነበርኮ! ማንም አልተከታተሰዎትም ። ማንም አልያዘዎትም ። ማንም አላወገዘዎትም ። እና ለምን ብለው ነው የተናዘዙልኝ ።»

«ስለእውነት ብዬ ነው የተናዘዝኩልህ ። አየህ.....አንድ አስሮ የያዘኝ ግመድ አለ ። ይህንን ግመድ እስካልበጠስኩት ድረስ ከእናንተ ጋር አብሬ ለመኖር ፣ የእናንተ ቤተሰብ አባል ለመሆን አይቻለኝም ። እኔ ቤተሰብ የሴ ለኝ ሰው ነኝ ። ከእናንተም ሆነ ከማንኛውም ሌላ ቤተሰብ ጋር ልገጥም አልችልም ። እኔ የማላስፈልግ ትርፍ ሰው ነኝ ። ያልታደልኩ መከረኛ ሰው ነኝ ። ይህችን ልጅ ለእንተ በጋብቻ በሰጠኋት ቀን የኔ ጉዳይ አለቀ ለት ። ልጅቷ ከእኔ ጋር ደስ ብሏት ኖረች ። አሁን ደሞ ከምታፈቅረው ሰው ጋር ነች ። በእናንተ በሁለታችሁ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ፍላጎት የለኝም። ፎሽለቫ ነኝ በማለት እስከዛሬ ድረስ በውሸት ስም ኖርኩ ። ኮዜት ከእኔ ጋር እስካለች ድረስ በዚህ የውሸት ስም ብጠራ ማንንም የሚ ጎዳ አልነበረም ። አሁን ግን በውሸት ስም ለመኖር አልችልም ። እና እውነቱን ለመናዘዝ ምን አስገደደህ.....? ምን ምክንያት አለህ.....? ስትል ጠይቀኸኛል ። ያስገደደኝ የጣዘ ሕሊናዬ ነው ። ፎሽለቫ ነኝ ብዬ በዚህ ውሸት ብገፋበት ኖሮ ከእናንተ ጋር አብሬ እኖር ነበር ። ሁሉም ነገር በሰ መረም ነበር ። ነገር ግን ሳይ ላዩን የተደሰትሁ መስዬ ውስጥ ውስጡን ተከፍቼ ለመኖር አልፈልግም ። እውነተኛ ደስታ ውስጣዊ ደስታ ነው ። ስለሆነም ከአሁን ወዲያ በውሸት ስም ለመጠራት አልፈለግሁም ።»

ትንፋሹን ወደ ውስጥ መለስና ቀጠለ ዣን ቫልዣ ፤ «በኑዛዜዬ ምክ ንያት ትንቂኝ ይሆናል ። እንደቅሌታም ሰው ትቆጥሩኝም ይሆናል ። ነገር ግን ራሴን በራሴ ለማክበር ከመናዘዝ የተሻለ ሌላ ዘዴ አላገኘሁም ። ምንም እንኳ የቀድሞ እስረኛ ብሆንም ሕሊና ያለኝ ሰው ነኝ ። ሕሊናዬ የማይፈቅ ደውን ለማድረግ አልፈልግም ። አየህ ሙሴ ማሪዩ..... በሕይወቴ ውስጥ ብዙ ፈተና ያርሶብኛል ። አንድ ሰው መጥፎ ስም ካለው ሌሎች ሳያ ውቁት በሱ መጥፎ ስም መበከል አይገባቸውም ። እናንተም በእኔ መጥፎ ስም መበከል አይገባችሁም ። ስለዚህ እውነቱን መናዘዝ ግዴታ ሆነብኝ ። በድሮ ጊዜ ለመኖር ያህል ብዬ ዳቦ ሠረቅሁ ። ዛሬ ደሞ ለመኖር ያህል ብዬ የሰውን ስም ለመስረቅ አልፈለግም ።»

«ለመኖር ያህል.....? ለመኖር ያህል ፎሽለቫ የሚለው ስም አያስፈል ጎትም» ሲል አቋረጠው ማሪዩ ።

@OLDBOOKSPDF

«ፎሽለቫ ነኝ ስል ኖሬ አንድ ቀን ፖሊስ መጥቶ ግን ቫልጣ ነህ ብሎ በእናንተ ፊት ቢያጋልጠኝ ኖሮ ምን ዓይነት ሀፍረት በተሰማኝ ነበር! አሁን ግን እውነቱን በመናዘዜ እፎይታ ተሰምቶኛል ።»

«አያቴ ወዳጆች አሉት ። በሕግ ፊት ይቅርታ እንዲደረግልዎ ለማድረግ እንችላለን» አለው ማሪዩ ።

«ዋጋ የለውም!» አለው ግን ቫልጣ ፤ «ግን ቫልጣ ሞቷል ተብሎ ስለታመነ ዋጋ የለውም ። ስው በሕይወቱ ሳለ እንጂ ሞቷል ተብሎ ከታመነ በኋላ የሚከታተለው የለም! በዚያ ላይ ሕሊናዬ እንጂ ሌላ የሚያስጨንቀኝ ነገር የለም!»

በዚህ ጊዜ በሩ ተከፍቶ ኮዜት ገባች ። እንቅልፍ አልጠገበች ፍሮ ዓይኖቿ አባብጠዋል ። ግን ቫልጣንና ማሪዩን አፈራርቃ አይታቸው ፤ «የፖለቲካ ወሬ ይዛችኋል መሰለኝ! እሱን ትታችሁ ከኔ ጋር ብትሆኑ ፍሮ የተሻለ በሆነ!» አለቻቸው ።

«የፖለቲካ ወሬ አይደለም ። የወረስኸውን ሀብት በምን ላይ ብናውለው ይሻላል ብለን ስንወያይ ነበር» አላት ማሪዩ ፤ እውነተኛውን አርእስተ ነገር ለመሸፋፈን ፈልጎ ፤ «እና ላንቺ የሚስማማ ውይይት ስላልሆነ ብቻችንን ብትተዩን.....»

«ግድ የለም ይስማማኛል ።»

«ላንቺ የሚሆን አይደለም ኮዜት..... ብቻችንን ተዩን ።»

«ግድ የለም ይስማማኛል ብዬሃለሁ ።»
«የማይሆን ነው ስልሽ!»

«ለምንድነው የማይሆነው? ከእናንተ ጋር ስመሆን እፈልጋለሁ ።»

«ብቻችንን መሆን አለብን ኮዜት ። እመኚኝና ብቻችንን መሆን አለብን ።»

ኮዜት ፊቷን ወደ ግን ቫልጣ መልሳ ፤ «ለምንድነው ከእኛው ጋር ቆዩ የማትሉኝ አባዬ.....? ለመሆኑ ፊትህ ለምን ገረጣ.....? እጅህን አመመህ እንዴ አባዬ?»

«ደህና ነኝ» አላት ።

«ትናንትና ማታ እንቅልፍ አልተኛህም!»

«ተኝቻለሁ ።»

@OLDBOOKSPDF

«ደህና ከሆንክስ ላመኻ» ብላ ግምባሯን ሰጠችው ። ግን ቫልገ ግምባሯን ላመው ።

«ፈገግ በል አባዬ» አለችው ።

ግን ቫልገ ፈገግ አለላት ።
«በይ አሁን ሂጅልን» አላት ማሪዩ ።

ኮዜት ከዚያ ይበልጥ ለመከራከር ስላልፈለገች ወጥታ ሔደች ። ማሪዩም በሩን ዘጋውና ፤«አዬ ኮዜት.....! እኔ የሰማሁትን ብትሰማ ኖሮ.....!» አለ ።

«ለአንተ ነው እንጂ እውነቱን የተናዘዝኩት ሰሺ አይደለም» አለው ግን ቫልገ ፤ «እንዳትነግራት ም ቃል እንድትገባልኝ አፈልጋለሁ ። የቀድሞ እስረኛ መሆኔን ብታውቅ ደንጋጤው ይገድላታል ። ደሞም እስረኛ መሆኑ ምን እንደሚመስል ታውቃለች ። አንድ ቀን ከባድ ሥራ እንዲሠሩ የተፈረዶባቸው የሕግ እስረኞች ታስረው ሲወሰዱ አይታለች ። እና እኔ የቀድሞ እስረኛ መሆኔን ብታውቅ.....!» ብሎ በዝምታ ያለቅስ ጀመር ። «ብሞት በተሻለኝ ነበር!» አለ ለራሱ እንደሚናገር ሰው ።

«እሺ አይዞዎት! ምስጢርዎን ለኮዜት አልነግራትም ። ቃል ገብቼል ዎታለሁ» አለው ማሪዩ ። ተጠል አድርጎም ፤ «ለኮዜት ያወረሷት ገንዘብ በጣም ብዙ ስለሆነ ከፈሉን መልሰው ቢወስዱት.....» አሰው ።

«አመሰግንሃለሁ» አለው ግን ቫልገ ፤ «ከአሁን ወዲያ ሁሉም ነገር ተጠናቅቋል..... ከአንድ ነገር በስተቀር ።»

«ምንድነው አሉ?»

«ኮዜትን እንዳንድ ጊዜ መጥቼ ባያት እወዳለሁ ። እንደ አባትና ልጅ ሆንን ለረጅም ጊዜ አብረን ስለኖርን ፈጽሞ ላላያት ለመኖር አልችልም ። ስለሆነም ፈቃድህ ከሆነ አልፎ አልፎ መጥቼ ብጠይቃት ደስ ይለኛል ።»

«በየቀኑም ቢሆን መጥተው ሊጠይቋት ይችላሉ ። እንዲያውም ኮዜት ደስ ይላታል ።»

ይህንን ከተነጋገሩ በኋላ ግን ቫልገ አመስግኖት ወጣ ።

— 2 —

ማሪዩ በሰማው ሁሉ መንፈሱ ተረበሸ ። ድሮም ቢሆን በግን ቫልገ ሕይወት አንዳች ስውር ነገር መኖሩን ይጠራጠር ነበር ። ያ ስውር ምስጢር ምን እንደሆነ አሁን ገባው ። በጋብቻቸውም ላይ ደስ የማይል ጥላ ጣለበት ።

«ፍቅር አሳውሮኝ ነበር ወይ! አለዚያ ይህ ሁሉ ምስጢር ሳይገለጽልኝ እንዴት ቀረ!» ሲል ያስብ ጀመር ።

@OLDBOOKSPDF

ፍቅር ዓይኑን ጋርዶበት በጎርቦ ማረፊያ ቤት የሆነውን ድራማ እንኳ ለኮዜት ሳይገልጽላት መቅረቱን አውን አስታወሰ ።

ለመሆኑ በጎርቦ ቤት የሆነውን ድራማ ለኮዜት ቢገልጽላት ኖሮ ፣ ግን ቫልግም የቀድሞ እስረኛ መሆኑን ቢገነዘብ ኖሮ በእሱ ላይ ለውጥ ያስከትል ኖሯል ወይ? ለኮዜት የነበረው ፍቅር ይቀንስ ነበር ወይ? ሳያገባትስ ይቀር ነበር ወይ?

እነዚህን ጥያቄዎች በአእምሮው ውስጥ አንስቶ ከጣለ በኋላ ፣ «ምንም ነገር ባልተቀየረም ነበር ። ኮዜትን እንደድሮው ባፈቀርኋት ነበር ። እሷን ከማግባት ወደኋላም ባላልሁ ነበር ። ስለዚህ አንዳችም የሚያስጸጽተኝ ነገር የለም» ሲል አሰበ ማሪዩ ።

ሆኖም ግን ቫልግ የቀድሞ እስረኛ ሆኖ መገኘቱ አውንም ቢሆን ዘገነነው ። «እኚህ ሰው ለመስረቅና ለመታሰር እንዴት ቻሉ? በሴላ በኩል ደሞ ለኮዜት ይህን ያህል ሀብት ሊያወርሷት እንዴት በቁ? ሀብቱንስ ከወ ዴት አገኙት?» እያለ ማሰላሰሉን ቀጠለ ፤ «ምስጢራቸውን እንዲናዘዙ ያስ ገደዳቸው ሰው የለም ። ታዲያ ለምን ተናዘዙልኝ? ሕሊናቸው ስላስገደዳ ቸው ብቻ ወይንስ ሴላ ምክንያት አለ?» መላው ነገር እንቆቅልሽ ሆነበት ።

በጎርቦ ማረፊያ ቤት በዝንድሬት ክፍል ውስጥ የሆነው ድራማ እን ደገና በአእምሮው ውስጥ ይመላለስ ገባ ። «ፖሊሶቹ ሲመጡ ፎሽለቫ ለምን ሸሸተው አመለጡ? ወንበዴዎቹን ከሕግ ፊት ለማቅረብ ሳይሞክሩ ለምን ቀሩ?» አሰና ፤ «እምን..... አውን ግባኝ ። ራሳቸው በሕግ ፊት የሚፈለጉ ስለነበሩ ከፖሊሶች ለማምለጥ ፈልገው ነው የሸሹት!» አለ ።

ቀጠለ የመላ ምት አስተሳሰቡን ፤ «በአመጹ ዕለት ወዴ ምሽጉ ለምን መጡ ለመሆኑ? ሰውጊያ ነው እንዳይባል በውጊያው አልተካፈሉም ። ታዲያ ምን ሊፈጥሩ መጡ? ምናልባት ግቮርን ፍሲጋ ነበር የመጡት? እን ደሱ ከሆነ ግቮር በአመጸኞቹ እንዲታሰረ አውቀው በእሱ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ አስበው መሆን አለበት!»

ግን ቫልግ ግቮርን ይዞ ወደ ትንሹ ምሽግ እንደወሰደውና ከዚያም በኋላ የተኩስ ድምጽ እንደተሰማ ትዝ አለው ፤ «አዎን ። የበቀል እርምጃ ለመውሰድ መሆን አለበት ፤ ሳይበቀሉትም አልቀሩም ። ወስደው ገደሉት! ብቻ..... እንዲህ ያሉ አኩይ ሰው ከሆኑ ከኮዜት ጋር ምን አገናኛቸው? እን ዴትስ ሊንከባከቧትና እንደ ልጅ ሊያሳድጓት ቻሉ? እንደሳቸው ያለ ወን ጀለኛና ኮዜትን የመሰለ መልአክ አብረው ሊኖሩ ፣ ሊጣጣሙ ይችላሉ ወይ?»

ማሪዩ ይበልጥ በተመራመረ ቁጥር እንቆቅልሹ ይበልጥ የማይፈታ ሆነበት ። ግን ቫልግ በየጊዜው እየመጣ ኮዜትን እንዲጠይቃት በመፍቀ ዱም ሳይጸጸትበት አልቀረም ። ሆኖም ቃሉን ለማጠፍ ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሰባት

ጭልምልምታ

— 1 —

በማግሥቱ ምሽት ላይ ጐን ቫልጐ ከአጎዝልኖርማ መኖሪያ ቦታ መጥቶ የምድረ ግቢውን አጥር በር አንኳኳው ። ባስክ እንዲጠባበቀው ተነግሮት ኖሮ የአጥሩን በር ከፍቶ አስገባውና «ወደ ፎቁ ለመውጣት ይፈልጋሉ ወይንስ በምድር ቤት ቢቆዩ ይመርጣሉ? መሲ ማሪዩ ናቸው እንድጠይቆት ያዘዙኝ» አለው ።

«በምድር ቤቱ እቆያለሁ» አለው ጐን ቫልጐ ።

ክፍሉ ዋሻ የመሰለና ርጥበት የበዛበት ነበር ። አቧራም ሰብሷል ። የሸረሪት ድር ደርቦበታል ። በአንድ ጥግ ጠርሙስ ተከምሮበታል ።

ባስክ የበራ ሻማ አምጥቶ በእሳት ማንደጃው መደርደሪያ ላይ አኖረ ውና ከዜትን ለመጥራት ወጥቶ ሔደ ። ጐን ቫልጐ ሶፋ ላይ ዘርፈጥ ብሎ ይጠባበቅ ገባ ።

«ለምንድነው ወደ ፎቁ አልወጣም ያልከው አባዬ?» አለችው ከዜት እንደገባች ፤ «ጠባይህን ባውቀውም እዚህ መጥቼ እንድቀበልህ በማድረ ግህ ሳልገረም አልቀረሁም ።»

«እዚህ ብሆን ይሻላል ብዬ ነው ።»

«ለማንኛውም እስቲ ሳመኝ አባዬ» አለችው ። ጐን ቫልጐ ዝም አላት ።

«ምን አጠፋሁ አባዬ? እስቲ ለማንኛውም ዛሬ እራት አብረን እን ብላ»

@OLDBOOKSPDF

«አራት በልቼ ነው የመጣሁት ።»

«እውነት አይመስለኝም ። ብቻ እራት ከእኛ ጋር ለመብላት ካልፈለ ግህም እፎቅ አንውጣና ከሙሌ ገርልናርማ ጋር ፥ ተግናኙ ። እሳቸው ይወቅ ሱልኛል ።»

«አላደርገውም ።»

ከዚት ግራ ተጋብታ ፤ «ለምን?» አለችው ፤ «ደሞም በዚህ አስጠሊታ ክፍል ውስጥ ለመቆየት ለምን እንደመረጥክ አልገባኝም ።»

«ጠባዬን ታውቂዋለሽ አመቤት፣ አንዳንድ ጊዜ ይሽው ኑኝ ።»

«አመቤ—ት? እሬን ነው አመቤት ብለህ የምትጠራኝ አባዬ?»

«አመቤት ለመሆን ፈለግሽ..... አመቤትም ሆነሻል ።»

«አመቤትነቴ ላንተ ነው እንዴ ታዲያ አባዬ?»

«አባዬ አትበዪኝ ።»
«አባዬ አትበዩ.....ኝ? ታዲያ ማን ልበልህ?»

«ሙሌ ገርን ወይም ሀዲረቁ ገርን ብለሽ ጥሪኝ አንጂ አባዬ አትበዪኝ ።»

«ከአሁን ወዲያ አባት አይደለህም፣ ይህ ሁሉ ምን ማለት እንደሆነ አልገባኝም ። ምን አጠፋሁ ለመሆኑ? ከእኛ ጋር አልኖርም አልክን ። ያዘጋ ጀሁልህን ከፍል አልፈልግም ብለህ ትተኸዋል ። ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ለመሆኑ?»
«ምንም አዲስ ነገር አልተፈጠረም ።»
«እንግዲያው ስምህን ለምን ቀየርክ?»

«አንቺስ ብትሆኚ ስምሽን ቀይረሽ የለም፣ ያንቺ ስም ማዳም ፖሚርሲ ሲሆን የኔ ስም ሙሌ ገን የማይሆንበት ምን ምክንያት አለ!»

«እኔስ ምኑም አልገባሽ ብሎኛል ። ፈጽሞ ተለውጠሀብኛል ።»

ዝም አሳት ገን ቫልገ ።

ፍቅሯን ለመግለጽ ያህል እጁን አንስታ አንገቷ ላይ አደረገችውና ፣ «ከኛ ጋር አብረሽን ኑር ነው የምልህ አባዬ ። ደስ ብሎን እንኖራለን» አለችው ።

«ባል ስላገባሽ ከአሁን ወዲያ አባት አያሻሽም» አሳት ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚት በዚህ ጊዜ ተናደደች ። «ምን ማለትህ እንደሆነ ጭራሽ ሊገባኝ አልቻልኩም!» አለችው ፣ «አባቱ ርሽላቫ እንዳልሆንክ ፀሉ ሙሴ ግን ብለሽ ጥሪኝ ትለኛለህ..... ከእኛ ጋር ኑር ስልህ አሻፈረኝ ትለኛለህ..... እና ስምንድነው የምታበሳጨኝ፣ የእኔ ደስታ አናደደህ ወይ፣ ወይንስ ለምንድነው እንደዚህ የምትሆንብኝ!»

የእኔ ደስታ አናደደህ ወይ ማለቷ ልቡን ጠቅ አደረገው ። «ከዚት..... የተደሰትሽ መሆንሽን እውቃለሁ ። የኔ ነገር ግን አልቋል» አላት ።

ከዚት አንገቱ ላይ ተጠመጠመች ። አሁም እቅፍ አደረጋት ። ከዚያ በኋላ ባርኔጣውን ሰቀም አድርጎ ተነሳ ።

«እና?» አለችው ።
«መሐዴ ነው ። እነሱም ይጠብቁሻል» ብሎ ተሰናብቷት ወጣ ።

ከዚት የባሰውን ግራ ተጋባች ።

— 2 —

ግን ቫልጋ በየቀኑ መጥቶ ከዚትን መጠየቁን ቀጠለ ። እሱ በሚመጣ በት ወቅት ማሪዩ ከዚያ አይገኝም ። ሆን ብሎ ወደሌላ ቦታ ይሄዳል ። ግን ቫልጋም ከዚትን ጠይቆ ከመሐዴ በስተቀር ከገርልኖርማ ጋር አይገናኝም ።

ጊዜው ውሎ ሲያድር አንዳንድ ለወጣት መክሰታቸውን ልብ ሳይል አልቀረም ግን ቫልጋ ። ስምሳሌ አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት ሲሔድ ከዚት በዚያ አለመኖርዋ ተነገረው ። አንድ ሰዓት ያህል ጠብቆ ሳያገኛት ወደ ቤቱ ተመለሰ ። በሌላ ቀን ደሞ ዋሻ በመሰለው ክፍል ውስጥ አሳት አለመነደዱን ልብ አለ ። በተሰምዶ ግን አሱ በሚመጣበት ጊዜ አሳት ይነድድ ነበር ። እነዲሁ በሌሳ ቀን ከዚትን ጥየቃ ሲመጣ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት መቀመጫዎች በዚያ ሰላልነበሩ ከዚትን ቁጭ መጠበቅ ግዴታ ሆነበት ። ወንበሮቹን ማን እንዳነሳቸው ከዚት ራሷ አታውቅም ነበር ። ነገር ግን ወንበሮቹ የተነሱት ያለምክንያት ይሆናል ብሎ አላሰበም ግን ቫልጋ ። «ምናልባት ማሪዩ ሊያገልሰኝ ፈልጎ ይሆናል» ሲል ተጠራጠረ ።

የግን ቫልጋን ጥርጣሬ የሚያባብስ ሌላም ነገር ተፈጠረ ። ከዚት ከግን ቫልጋ የወረሰችው ሀብት ሳይነካ መቆየቱን ሰማ ። እንዲያውም ማሪዩና ከዚት ከገርልኖርማ በሚያገኙት ሦስት ሺ ፍራንክ ብቻ እንዲኖዳ ያፉ ማሪዩ ለከዚት ሃሳብ እንዳቀረበላት ከዚት ራሷ ለግን ቫልጋ ነገረ ችው ። «ለከዚት ያወረስኳት ሀብት በሕጋዊ መንገድ ያላገኘሁት ቢመስ ልው ነው» ሲል አሰበ ግን ቫልጋ ።

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ሁሉ ምክንያት ቅር ተሰኝቶ ጉብኝቱን አቋረጠ ጥን ቫልጥ ። በመደዳ ሦስት ቀን ሳይመጣ በመቅረቱም ከዚት ታምሞ ይሆናል የሚል ስጋት ሰላደረባት ኒኮሌት ሐዳ እንድታይ ላከቻት ። ኒኮሌት ደህንነቱን ስትጠይቀው ፤ «ደህና ነኝ ። ሳልመጣ የቀረሁት ሥራ ስለበዛብኝ ነው ። ሥራዬን እንደጨረስኩ እመጣለሁ ። ደሞም ጉዞ ለመሔድ ስላሰብኩ ከዚት ስጋት እንዳያድርባት ንገሪያት» ሲል መልሶ ላካት ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ስምንት

ውድቅት ጭለማና ንጋት

— 1 —

የጣን ቫልጣ ጥርጣሬ መሠረተ ቢስ ስልነበሪም ። ማሪዩ በእርግጥም ጣን ቫልጣን ሊያገልሰው ፣ ከኮዜት ሊያርቀው ጥረት ያደርግ ነበር ። ይሽ ውም በግሃድ ሳይሆን በረቀቀ ዘዴ ነበር ። ለምሳሌ ጣን ቫልጣና ኮዜት እንዳይገናኙ በሚፈልግበት ጊዜ ኮዜትን ድሮ የፍቅር ሕይወት ያሳለፉበትን ቦታ መልሰን እንየው በሚል ሰበብ ወደ ፕሎሚ ገጸና ይዟት ይሬዳል ። ወይንም የአባቴን መቃብር ላሳይሽ በሚል ሰበብ ወደ ቬርኖ ይዟት ይጓ ዛል።

ማሪዩ ጣን ቫልጣን ከኮዜት ሊያገልሰው የፈለገው አንደኛ ፣ በጣን ቫልጣ ኑዛዜ ምክንያት ፣ ሁለተኛም ስለሱ ድርጊት ቡትጨማሪ በዩረሰው መረጃ ምክንያት ነበር ። እንደአጋጣሚ ሆኖ በቀድሞ ጊዜ የላፊት ባንክ ሠራተኛ የነበረ ሰው አግኝቶ በምስጢር ፣ ሚያዝ ወራ ሰማ ። ይሽውም ሰኮ ዜት ያወረሳትን ገንዘብ በ ሂመለከት ነበር ። ይህንን ገንዘብ አንድ ፍራንክ እንኳ ሳይጐድል ለሚገባው ሰው ሊመመለስ ሃሳብ ነበረው ፤ በእርግጥም ከሴላ ሰው የተዘረፈ ሀብት ነው ብሎ አምኖ ነበረና ። ኮዜት ግን ስለ ጣን ቫልጣ ኑዛዜም ሆነ ማሪዩ ስለሰበሰበው ተጨማሪ መረጃ የምታውቀው ነገር አልነበረም ።

ጣን ቫልጣ በበኩሱ ኮዜትን ለማየት አሁንም ይፈልጋል ። እሷን ሊመጠየቅ ብሎ ከቤቱ የሚወጣበት ጊዜ አለ ። ከአንገርልኖርማ ቤት ደርሶ ፣ ነገር ግን ከቤት ሳይገባ የሚመለስበት ጊዜ አለ ። ግማሽ መንገድ ተጉዞ ወደ ቤቱ የሚመለስበት ጊዜም አለ ። ሆድ ብሶት የሚያለቅስበትም ወቅት አለ ። እንዲሁ በስቀቅን ሲኖር ሳለ እህል ውሃ አስጠላው ። ምግብ ሙቢላ ዝን ተወው ። ከቤት መውጣቱን አቆመ ። ከዚያም በኋላ የአልጋ ቁራኛ ሆነ ።

@OLDBOOKSPDF

ሁኔታውን የተገነዘበችውና ምግብም የምትሠራለት አሮጊት ሴትዮ አንድ ቀን ከፍሉ ውስጥ ገብታ «ምነው ምግብ ሳይቀምሱ እደሩ!» ስትል ጠየቀችው ፤ ትናንትና ማታ ያቀረበችለትን አስመጣላቱን አይታ ።

«ውሃ ጠጥቻለሁ..... ይበቃኛል» አላት ።

አሮጊቷ የሕንጻው በረኛ ሚስት ነበረች ። ግን ቫልጣ አንድ ሳምንት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ከሰነበተ በኋላ ፤ «ፎቁ ላይ ያሉት ዶጉ ሽማግሌ ከአልጋቸውም አይነሱም» ስትል ለባሏ ነገረችው ፤ «ምግብ አይቀምሱም ። ለረጅም ጊዜ በሕይወት የሚቆዩ አይመስለኝም ። ሰውዬው አንዳች የሚያሳዝን ነገር ደርሶባቸዋል ። ምናልባት የልጃቸው ጋብቻ ያልተሳካ ቢሆን ነው»

«ሀብታም ከሆኑ ሐኪም ይጠራላቸዋል ። አለዚያ ምን ይደረጋል!» አላት በረኛው ባሏ ።

«የሚያሳዝን ነው ። ሰውዬው ሰብሰብ ብለው የሚኖሩ ናቸው ።»

እንደአጋጣሚ ሆኖ የአካባቢው ሐኪም በቤታቸው አጠገብ ሲያልፍ አግኝታው ግን ቫልጣን ወጥቶ እንዲያየው ለመነችው ። «ሁለተኛው ፎቅ ላይ ናቸው..... ዘራቸው ሁል ጊዜም ክፍት ስለሆነ ገባ ብለው ቢጠይቁቸው ዶክተር.....»

ሐኪሙ ወደ ግን ቫልጣ ክፍለ ወጥቶ አነጋግሮት ከፎቁ ሲወርድ አሁንም አሮጊቷ አገኛቸውና ፤ «እንዴት ናቸው ዶክተር!» ስትል ጠየቀችው ።

«ሰውዬው በጣም ታምመዋል» አላት ።
«ምናቸውን ነው ያመማቸው!»

«በሽታቸው ይህ ነው ለማለት አይቻልም ። በጣም የሚያፈቅሩትን ሰው ያጡ ይመስላል ። በጣም የሚያፈቅሩትን ሰው ማጣት ከሞት ለያደርስ ይችላል ።»

«ምን አሉዎት!»
«እሳቸውማ ጤና ነኝ ባይ ናቸው ።»
«እና ተመልሰው ይመጣሉ ዶክተር!»

«አዎን ፣ ተመልሼ እመጣለሁ ። ነገር ግን እኔ ብቻ ሳልሆን ያጡትም ሰው መምጣት ይኖርበታል ።»

— 2 —

እየተዳከመ ሔደ ግን ቫልጣ ። ከአልጋው መነሳት እንኳ ያቅተው ጀመር ። ሆኖም አንድ ቀን እንደምንም ታግሎ ተነስቶ የሥራ ልብሱን ለባበሰ ። ሻንጣውን ከፍቶ የከዜትን የድሮ ልብሶች አወጣቶ

@OLDBOOKSPDF

አልጋው ላይ ዘረጋቸው ። አቡነ ሚሪዬል የሰጠት የሻማ መቅረዞች ቀድሞ በነበሩበት በአሳት ማንደጃው ላይ ባለው መደርደሪያ ነበሩ ። ሁለት ሻማ ዎች ከጠረጴዛው ኪስ አውጥቶ መቅረዞቹ ላይ ሰካቸው ። ቀን ቢሆንም አበራቸው ።

እንቅስቃሴው የባሰውን ስላደከመው ወንበር ላይ አረፍ አለ ። ወንበሩ ከመስታውቱ ፊት ለፊት ነበር ፤ አንድ ቀን ማምጠጫ ላይ የነበረውን የኮዜ ትን ጽሑፍ ያነበበበት መስተዋት ። ፊቱን በመስተዋቱ ቢያየው የሴላ ሰው ፊት መሰለው ። ዕድሜው በዚህ ጊዜ ሰማንያ ዓመት ደርሶ ነበር ። ይሁን እንጂ ከኮዜት ሠርግ በፊት የአምሳ ዓመት ጐልማሳ ነበር የሚመ ስል ። ከዚያ ወዲህ በነበረው አጭር ጊዜ ውስጥ ነው ግርጅፍጅፍ ያለው ። ግንባሩ ላይ የሞት ጥላ አርፎበት አየ ። ጉንጮቹ ሟሽዋል ። የፊቱ ቆዳ አፈር መስሏል ። የአፉ ጥግ ከርቦ ሠርቷል ።

ወደ ጠረጴዛው ተጠግቶ ብዕር አንስቶ ይጽፍ ጀመር ፦—

«ኮዜት..... ምርቃቱ ይድረስሽ ። ባልሽ እኔን ማግለሉ ትክክል መሆ ኑን ልገልጽልሽ እወዳለሁ ። ባልሽ በጣም ጥሩ ሰው ነው ። እኔ ከሞትኩ በኋላም ቢሆን ሁለታችሁ ተፋቀሩ ። ይሁን እንጂ ባልሽ አንድ የተሳሳተ በት ነገር አለ ። ያወረስኩሽ ግንዘብ የጥቁር መስተዋት ጌዋ የሚሠራበትን ዘዴ ፊልስሜ ያፈራውት እንጂ በሴላ መልክ ያገኘሁት አይደለም ። ስለዚህ ይህ ሀብት አንጡራ ሀብትሽ መሆኑን ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ ።»

ይሀንን ከጻፈ በኋላ ብዕሩ ከእጁ አምልጦ ወደቀ ። እሱም ያለቅስ ጀመር ። «ዐቢቃ..... ሁሉ ነገር አብቅቷል» አለ ራሱ ሰራሱ ፤ «ደግሜ ሳላያት ሞት ሊቀድመኝ ነው ። ወይኔ.....! ምነው ለመጨረሻ ጊዜ ባየኋት! ድም ጿን በሰማሁ! እጅዋን በነካሁ! ከዚያ በኋላ ብሞትም ባልቆጭኝ» ሲል የክፍሉ በር ተንኳኳ ።

— 3 —

በዚያው ቀን ምሽት ኮዜት ከሠልኖርማ ጋር አትክልቱ ቦታ ውስጥ ስትንሸራሸር ሳለች ማሪዩ በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ ነበር ። ባስክ ማሪዩ ዘንድ ጉቡዙ «የሚፈልጎት ሰው አለ» ብሎት አንድ ማስታወሻ ሰጠውና ወጣ ።

ማስታወሻው በሸካራ ወረቀት የተጻፈና በቅጡ ያልታጠፈ ነበር ። ደሞም ትምባሆ ትምባሆ ይሸትታል ። ይህ ሽታ ማሪዩን አንድ ነገር አስ ታወሰው... ገርንድሬትና ይኖርበት የነበረው አነስተኛ ክፍል ። ዘርግቶ ቢመለከተው ማስታወሻው ብዙ ግድፈቶች አሉበት ። መልእክቱ ግን እን ዲህ የሚል ነበር ፦—

@OLDBOOKSPDF

ሙሴ ባሮን፦—የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ተሰጥዎ ቢኖረኝ ኖሮ እኔም ባሮን ቱናር በተሰኘሁ ነበር ። የሳይንስ አካዳሚም አባል በሆንሁ ነበር ። ነገር ግን አይደለሁም ። ውለታ ትውልልኛለህ ብዬ በማሰብ ነው ይህንን ማስታወሻ የጻፍኩልህ ። ይሁን እንጂ በብላሽ ውለታ ዋልልኝ ማለቴ አይደለም ። በበኩሌ ስለ አንድ ሰውዬ በምስጢር የምነግርህ አለኝ ። የሰውዬው ጉዳይ አንተንም ጭምር የሚመለከት ጉዳይ ነው ። ይህንን ምስጢር ላካፍልህ ፈቃደኛ ነኝ ። ማዳም ባሮን ከትልቅ ቤተሰብ የምትወለድ ስለሆነ ይህ ሰውዬ ከእናንተ ዘንድ መወገድ ይገባዋል ፤ ወንጀለኛ ነውና።

መልስህን እየተጠባበቅሁ ነኝ ።
ከአክብሮት ጋር ።
ቱናር ።

ማሪዬ ይህንን ማስታወሻ አንብቦ ሲጨርስ ሰውዬው ማን እንደሆነ ገባው ። መጥሪያውንም ያወል ጠረር አደረገው ። ባስክ ሊታዘዘው መጣ ።

«ሰውዬውን አስገባው» አለው ማሪዬ ።

ሰውዬው ተጠርቶ ገብቶ ቢያየው ያሰበው ሰውዬ አልሆንልህ አለው ። አጭንጫው ወፈር ያለ ፥ አረንጓዴ ቀለም ያለው መነጽር ያደረገ ፥ ግራጫ ጸጉሩ ሰው ሠራሽ የመሰለ ፥ ከሳይ እስከታች ጥቁር ልብስ የለበሰ ፥ አሮጌ ባርኔጣ በእጁ የያዘ ፥ ጀርባው ጉበጥ ያለ ፥ ኩቱ የሰፋበት ፥ ሽማግሌ ሰው ሆኖ አገኘው ።

ብዚያን ጊዜ በፓሪስ ከተማ ውስጥ የሰዎችን አለባበስና ገጽታ በመለወጥ የታወቀ አንድ አይሁዳዊ ነበር ። እኩይዎችን በጎ ሰዎች አስመስሎ የማቅረብ ተሰጥዎ ነበረው ። ይህንን የሚያደርገው ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን እንጂ ለዘለቂታው አልነበረም ። በቀን ሠላሳ ሱ ያስከፍላቸዋል የለወጣቸውን ሰዎች ። የሌሰው የልብስ ዓይነት አልነበረም ። የዳኞች ልብስ..... የካህናት ልብስ..... የባንከኞች ልብስ..... የጦር ሰዎች ልብስ..... የብዕር ሰዎች ልብስ..... የፖለቲከኞች ልብስ.....

የፓሪስ ኪስ አውላቂዎችና ሌሎች ወንጀለኞች ሌላ ሰው መስለው ለመታየት ሲፈልጉ አይሁዳዊው ዘንድ መጥተው የፈለጉትን ዓይነት ልብስ በቀን ሠላሳ ሱ ከፍለው ይሔዳሉ ። በማግሥቱ ልብሱን መልሰው አምጥተው ለአከራያቸው ይሰጡታል ። ያምናቸዋል ። ያምኑታል ። ይሁን እንጂ ልብሶቹ በሰዎቹ ልክ የተሰፉ ባለመሆናቸው አንዳንዴ ይጠቧቸዋል ። አንዳንዴ ደሞ ይሰፉባቸዋል ።

ማሪዬ ዘንድ የገባው ሰውዬ አይሁዱ ዘንድ ሔዶ ሌላ ሰው መስሎ የመጣ ነበር ።

«ምን ትፈልጋለህ» ሲል ጠየቀው ማሪዬ ኮስተር ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

«ከረጅም ጊዜ በፊት የተገናኘን ይመስለኛል» አለው ሰውዬው ፈገግ ብሎ ፤ «መጀመሪያ በልዕልት ባግራሲዮ ቤት ፣ ቀጥሎም በመስፍን ዳምብረ ቤት የተገናኘን ይመስለኛል ።»

«ልዕልት ባግራሲዮ ወይም መስፍን ዳምብረ የሚባል ሰው አላውቅም» አለው ማሪዩ ፤ «በእነዚህ ባልሀቸው ሰዎች ቤት ተገኝቼም አላውቅ!»

«እንግዲያውስ በሻቶብርየ ቤት መሆን አለበት የተገናኘነው ። ሻቶብርየን ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ ።»

ማሪዩ የባሰውን ፊቱን አኮሳትሮ ፤ «ከሻቶብርየ ዘንድ ለመገኘት ዕድል ያገኘሁበት ጊዜ የለም ። ይልቁንስ ወዴ ቁም ነገሩ ብንመለስና ምን ፍለጋ እንደመጣህ ብትነግረኝ.....»

«ስማኝ ሙሴ ባሮን.....» አለው ሰውዬው ፤ «በአሜሪካን አገር ከፓናማ አቅራቢያ ባለ ወረዳ ውስጥ ላ ገናያ የተባለ ሠፈር አለ..... ወርቅ የሚታፈስ በት ሠፈር.....»

«ለምንድን ነው ይህንን የምትነግረኝ?»

«ባለቤቴንና ሴት ልጄን ይዤ ወደ አሜሪካን አገር ሔጄ ላ ገናያ በተባለው ሠፈር ለመኖር እሻለሁ ።»

«ይህ ታዲያ ለኔ ምኔ ነው?»
«ማስታወሻዬን አልተመለከትኸውም መሰለኝ!»
«የምትፈልገውን ባጭሩ ንገረኝ» አለው ማሪዩ ።

«መልካም..... አንድ የምሸጥልህ ምስጢር አለኝ ።»

«እኔን የሚመለከት?»
«አዎን ።»
«ምንድነው ምስጢሩ?»

«ዋጋ በማትከፍልበት መረጃ ልጀምርልህ.....» ብሎ ፤ «ሙሴ ባሮን..... በቤትህ ውስጥ ሴባና ነፍስ ገዳይ የሆነ ሰው አለ» አለው ።

ማሪዩ ተንቀጠቀጠ ። «በእኔ ቤት? ተሳስተሃል!» አለው ።

«በገዛ ቤትህ ውስጥ ቀጣፊ ሴባና ነፍስ ገዳይ የሆነ ሰው አለ ብዬሃለሁ ። ይህ ሰው እውነተኛ ስሙን ደብቆ በሌላ ስም እየተጠራ ይኖራል ። እውነተኛ ስሙን ልነግርህ ነኝ ። ለዚህም አንዳችም ዋጋ አላስከፍልህም ።»

«እየሰማሁህ ነኝ ።»

@OLDBOOKSPDF

«አውነተኛ ስሙ ግን ቫልጊ ይባላል ።»
«ምስጢር ያልከው ይሽንን ነው? ይህ ከሆነ ለኔ ምስጢር አይደለም ። ቀደም ብዬ የማውቀው ነው ።»

«ማንነቱን ደሞ ልነግርህ ነኝ..... አንዳችም ጥጋ ሳላስከፍልህ ።»

«እሺ ቀጥል ።»
«ግን ቫልጊ የቀድሞ እስረኛ ነው ።»

«ይህንንም ቀደም ብዬ የማውቀው እንጂ ለኔ ምስጢር አይደለም ።»

«እሁን እኔ ስለነገርኩህ ነው እንጂ ቀደም ብለህ የምታውቀው አይመስለኝም ።»

«ቀደም ብዬ የማውቀው ነው ብዬሃለሁ ።»

የማሪዬ መልስ በሰውዬው ልብ ቁጣ አሳደረበት ። ሆኖም ፈገግ ብሎ ቀጠለ ፤ «በዚህ ጉዳይ እለመግባባት እንዲነሳ አልሻም» አለው ፤ «ለማን ኛውም ብዙ ስውር ነገር እንደማውቅ እንደተረዳህ አምናለሁ ። ቁጥሬ የም ነግርህ ምስጢር እንተ የምታውቀው አይደለም ። ይሽውም ባለቤትህ የወ ረሰችውን ሀብት የሚመለከት ነው ። ሀያ ሺ ፍራንክ ልትከፍለኝ ፈቃደኛ ከሆንክ በበኩሌ ምስጢሩን ልገልጽልህ ፈቃደኛ ነኝ ።»

«እሱንም ምስጢር አንተ ሳትነግረኝ ደርሼበታለሁ» አለው ማሪዬ ።

«ምናልባት የጠየቅሁህ ዋጋ በጣም ከፍተኛ ከሆነብህ ወደ አስር ሺ ፍራንክ ዝቅ ሳደርገው ፈቃደኛ ነኝ ። »

«ምስጢሩን ሳትነግረኝ በፊት ደርሼበታለሁ ብዬሃለሁ ።»

«ሙሴ ባሮን..... ችግረኛ ሰው ነኝ ። ባይሆን ሀያ ፍራንክ እንኳ ቸረኝና እውነተኛውን ምስጢር ሳውጣልህ ።»

«ምስጢር ያልከው ለኔ ምስጢር አይደለም ። ግን ቫልጊ የተባለውን ስም እንደማውቀው ሁሉ ፣ ያንተንም ስም እንደማውቀው ሁሉ ፣ የገንዘቡ ንም ምስጢር ይህና አድርጌ አውቀዋለሁ ።»

«ያንተንም ስም እንደማውቀው ሁሉ!»
«አዎን ።»
«አሃ...! ግባኝ በጻፍከልህ ማስታወሻ ላይ ቱናር መሆኔን ስለገለጽ ሁልህ ነው ስሜን ያወቅኸው ።»
«.....ዲዬ» አለው ማሪዬ ።
«ምንነ»

@OLDBOOKSPDF

«ቴናርዲዬ»
«ማን ነው ደሞ ቴናርዲዬ?»

«ደሞም ገንዳሬት ተጠለሀ ትጠራለህ ። ሩባንቱ..... ጣንፍሎ..... ዶን አልቫሬዝ..... ሚስትሬስ ባለዛርድ..... ሰምሽህ ብዙ ናቸው!»

«ሚስትሬስ ምን?»

«በሞንፈርመይ የመንገደኞች ማረፊያ ሆቴል እንደነበረህም አውቃለሁ ።»

«ፈጽሞ ውሸት ነው!»
«ቴናርዲዬ መሆንክን በድጋሚ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ ።»

«ፈጽሞ አልቀበለውም!»

«ደሞም አታላይ ሰው ነህ!» አለውና ማሪዬ ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ወረወረለት ።

ቴናርዲዬ ምን ጊዜም ለገንዘብ የሚሰገበንብ ሰው ስለሆነ ማሪዬ የወረወረለትን ገንዘብ ተመልክቶ ደስ አለው ። «አምስት ሙት ፍራንክ.....! እመሰግናለሁ መሲዬ ባሮን» አለው ። ከዚያም በኋላ እውነተኛ ማንነቱን ሕጋለጠ ። አረንጓዴ መነጽሩን ፣ በአጥን ሚው የሰካቸውን ሳባዎችና ፊቱን ለመቀየር ያደረጋቸውን ሌሎች መሸፋፈኛዎች ከፊቱ ሲያነሳቸው በእርግጥም የድሮው ቴናርዲዬ መሆኑ ግልጽ ሆነ ።

«መሲዬ ባሮን..... በእርግጥም ቴናርዲዬ ነኝ» አለው ። ይህንን ይበል እንጂ በልቡ በጣም ሳይገረም አልቀረም ። «ቴናርዲዬ መሆኔን በምን አወቁ? ስሰ ግን ቫልገ ይህን ያህል መረጃ ከወዴት ስበሰበ? አምስት መቶ ፍራንክ ለኔ መስጠቴስ ምን ትርጉም አለውን» ሲል አሰበ ቴናርዲዬ ።

ማሪዬና ቴናርዲዬ በአንድ ወቅት ጐረቤት ሆነው ቢኖሩም ቴናርዲዬ ማሪዬን አይቶት አያውቅም ። በእርግጥ ሴት ልጅቸ ማሪዬ የተባለ ወጣት ጐረቤታችን ነው ሲሉ ነግረውታል ። በግባር ግን አይቶት አያውቅም ። አሁንም ቢሆን መሲ ባሮን ብሎ የሚጠራው ሰውዬ የድሮው ጐረቤቱ ማሪዬ መሆኑን ፈጽሞ አያወቅም ።

ይሁን እንጂ ከሠርጉ ቀን ወዲህ በልጁ በአዘልማ አማኮኝነትና ቦራ ስም ክትትል ብዙ ነገር ለማወቅ ችሎ ነበር ። ሰምሳሉ በከርሰ ምድር ያገኘው ሰውዬ ግን ቫልገ እንደነበረ ፣ ማዳም ባሮን ፖሜርሲ የተባለችው ከዜት መሆኗንና ሌላም ብዙ መረጃ ስመለከለብ ቻለ ።

@OLDBOOKSPDF

ማሪዩ በበኩሉ ቴናርዲዬ እኩይ ሰው በመሆኑ ቢያዝንም የአባቱን ባለውለታ ከረጅም ጊዜ ፍለጋ በኋላ እንደገና ሲያገኘው በልቡ ደስ ሳይለው አልቀረም ።

«ስምህ ቴናርዲዬ መሆኑን ነግሬሃለሁ ። አሁን ደሞ ስለውርሱ ገንዘብ ምስጢር ነው ያልከውን ልንገርህ» አለው ማሪዩ ፤ «ምስጢሩን ከአንተ ይበልጥ እኔ እንደማውቀው ላሳምንህ እወዳለሁ ። አንተ እንዳልከው ሁሉ ዣን ቫልዣ ሌባና ነፍሰ ገዳይ ናቸው ። ከአንድ ባለ እንዱስትሪ ከፍ ያለ ገንዘብ ሰርቀዋል ። የፖሊስ ተቆጣጣሪ የነበረውን ጣቪርን የገደሉት እኚሁ ዣን ቫልዣ ናቸው ።»

«የምትናገረው ሁሉ አልገባኝም» አለው ቴናርዲዬ ።

«አትቸኩል..... እንዲገባህ አደርጋለሁ» አለና ቀጠለ ማሪዩ ፤ «አየህ..... በ1822 ዓ.ም. በፓ ዱ ካሌ ክፍለ ሀገር የሕግ አስረኛ የሆነ አንድ ሰውዬ ነበር ። ይህ የሕግ አስረኛ በኋላ ጊዜ ሕይወቱን አድሶ ሙሴ ማድሌን በተባለ ስም ይጠራ ነበር ። የጥቁር መስተዋት ጌጥ ቦመስራት ረገድ የታወቀ ባለእንዱስትሪ ሆነ ። ያለፈለት ከበርቴ ወጣው ። ድሆችን ይረዳ ነበር ። ሐኪም ቤትና ትምህርት ቤት ለአገሬው ሕዝብ በማሠራት የታወቀና የተከበረ ሰው ሆነ ። ከንቲባ ለመሆንም በቃ ። ቀደም ብሎ በአስር ቤት ሳለ የሚያውቀውና በኋላም ከአስር ቤት የተፈታ አንድ ሰውዬ ማድሌንን በወንጀል ድርጊት ከሶ አስያዘው ። ማድሌን ሲያዝ ይህ ሰውዬ ወዲ ፓሪስ መጥቶ በተጭበረበረ ፊርማ አማካኝነት ከላፊት ባንክ ከግማሽ ሚሊዮን ፍራንክ በላይ የሚሆን ሀብት አውጥቶ ወሰደ ። ይህንን መረጃ ያገኘውት በላፊት ባንክ በገንዘብ ያዥነት ይሠራ ከነበረ ሰው ስለሆነ እውነተኛነቱ የሚያጠራጥር አይደለም ። ይህ ገንዘብ የማድሌን ሀብት ነበር ። የማድሌንን ሀብት አጭበርብሮ የወሰደውም ይኸው የቀድሞ አስረኛ ነው ። በሌላ አንጋገር ዣን ቫልዣ ናቸው ።» አሰውና ቀጠለ ማሪዩ ፤

«ስለዣን ቫልዣ የነገርኩህ የማውቀውን ነው ። ጣቪርን በጥይት ደብድበው ነው የገደሉት ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እኔ ራሴ በቦታው ነበርኩ ።»

«ሙሴ ባሮን..... በትክክለኛው ጐዳና ያለህ አልመሰለኝም» አለው ቴናርዲዬ ።

«እንዴት? እውነተኛውን ሁኔታ ስገልጽልህ አታምነኝም!»

«እውነተኛው ሁኔታ እንደሱ አይደለም ። ዣን ቫልዣ ማድሌንን አልዘረፈም ። ጣቪርንም አልገደለም!»

«ይህንን ለማለት ምክንያት አለህ?»

@OLDBOOKSPDF

«ሁለት ምክንያቶች አሉኝ ።»
«እንስማቸዋ!»

«ጎን ቫልጣ የማድሌንን ገንዘብ አጭበርብሮ ለመውሰድ አይችልም ነበር ። ይኸውም ጎን ቫልጣና ማድሌን አንድ ሰው እንሺ ሁለት የተለያዩ ሰዎች አይደሉምና!» አለውና «ሁለተኛም ፣ ጎን ቫልጣ ጎቬርን አልገደለውም ። ምክንያቱም ጎቬርን የገደለው ጎቬር ራሱ ነውና!» ሲል የሚያውቀውን ነገረው ።

«ለዚህ ሁሉ ማስረጃ አለህ?»

«አዎን..... የተጨበጠ ማስረጃ አለኝ!» ብሎ ከኪሱ ትልቅ አምቦሉክ አውጥቶ ሰጠው ።

አምቦሉኩ ውስጥ ሁለት ጋዜጦች ነበሩበት ። አንደኛው የሐምሌ 25 ቀን 1823 ዓ.ም. «ድራፓ ብላ» ወይም ነጭ ባንዲራ የተባለው ጋዜጣ እትም ነበር ። ይህ ጋዜጣ ማድሌንና ጎን ቫልጣ የአንድ ሰው ስሞች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነበር ።

ሁለተኛው የሰኔ 15 ቀን 1832 ዓ.ም. የ«ሞኒተር» ጋዜጣ እትም ሆኖ ጎቬር ከሴን ወንዝ ውስጥ ዘልሎ ገብቶ የራሱን ሕይወት ማጥፋቱን የሚያረጋግጥ ነበር ።

ማሪዩ ጋዜጦቹን ከነበበ በኋላ ዜናውን ሙሉ በሙሉ ተቀበለው ። በላፊት ባንክ ይሠራ የነበረው ገንዘብ ያሻ የሰጠው መረጃም ትክክል አለ መሆኑንና እሱንም እንዳሳሳተው ተረዳ ። ጎን ቫልጣ ሌባና ነፍሰ ገዳይ አለመሆኑን ሲገነዘብ እጅግ በጣም ደስ አለው ። «እኚህ ሰው ታላቅ ሰው ናቸው!» አለ ፤ «ያ ሁሉ ሀብት በአርግጥም እንጡራ ገንዘባቸው ነቦር ። ጎቬርንም አልገደሉትም.....ምረመታል! እኚህ ሰው የአንድ ፊት ጀግና ፣ በሌላ ፊት የተቀደሱ ሰው ናቸው!»

«የተቀደሰ አይደለም ። ጀግናም አይደለም ። ጎን ቫልጣ ነፍሰ ገዳይና ሌባ ነው» አለው ቴናርዲዬ ።

«እንዴት? ምን ሰማለት ፈልገህ ነው?»

«ጎን ቫልጣ ማድሌንን ባይዘርፍም ሌባ ነው ። ጎቬርን ባይገድልም ነፍሰ ገዳይ ነው ።»

«ከአርባ ዓመታት ቦፊት ጸቦ ሰርቀው ታስረው ሰለንበርና በኋላም ተጸጽተውና ክሰው በጎ ሰው ሆነው በመኖራቸው ነው ሌባ ብለህ የምትጠራቸው ?»

@OLDBOOKSPDF

«እውነተኛ ሴባና ነፍሰ ገዳይ ነው ሙሴ ባሮን ። የማውቀውን ነው የምነግርህ ። ይህ ግን በምስጢር ደረጃ ያለ እንጂ በገሃድ የታወቀ አይደለም ። ይህንን ምስጢር ስገልጽልህ ይህን ያህል ከፈለኝ አልልህም ። የመሰለህን ዋጋ ትከፍለኛለህ» አለውና ፤ «መቆሙ ስለደከመኝ እንድቀመጥ ብትፈቅድልኝ» አለው ። ሁለቱም ቆመው ነበር የሚነጋገሩት ። አሁን ግን ወርደው ወንበር ያዙ ። ቴናርዲዬም ወጉን ቀጠለ ፤ «ሙሴ ባሮን—ከአንድ ዓመት በፊት ፥ በሰኔ 6 ቀን 1832 ዓ.ም. ይህም ማለት ሕዝባዊ አመጽ በተነሳበት ወቅት መሆኑ ነው ፥ አንድ ሰውዬ በፓሪስ ከርሰ ምድር ይገኝ ነበር ። በሆነ ምክንያት ሰውዬው በከርሰ ምድር ውስጥ ተደብቆ ይኖር ነበር ። የከርሰ ምድሩ መግቢያ በር ቁልፍ በእጁ ነበር ። ቀኑን ልድገመውና ሰኔ 6 ቀን ነበር ። ምናልባት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሳይሆን አይቀርም ። ይህ ሰውዬ ድምጽ ይሰማል ። በጣም ተገርሞ ድምጼን እጥፍት ይጠባበቅ ጀመር ። ወዲ እሱ የሚመጣ ሰው ኩቴ መኖሩን ተገነዘበ ። ሰውዬው በጀር ባው አስከሬን ተሸክሟል ። ሰውን ገድሎ ነው አስከሬኑን የተሸከመው ። ሰውዬውን የገደለውም ግንዘቡን ሲዘርፈው እንደነበረ የታወቀ ነው ። ከዚያ በታ ራቅ ብሎ የሰገራ ማጥ ነበር ። ነፍሰ ገዳዩ አስከሬኑን ማጡ ውስጥ ሊጥለው ይችል ነበር ። ነገር ግን የፍሳሽ አገልግሎት ሠራተኞች አስከሬኑን አግኝተው እንዳይከታተሉት በመፍራት አስከሬኑን ተሸክሞ ወጥቶ ወንዝ ውስጥ መጨመሩን መረጠ—»

ማሪዬ ይህንን ሲሰማ ከፍተኛ የሆነ የማወቅ ጉጉት ስላደረበት ወን በሩን ወደ ቴናርዲዬ ወንበር አሰጠጋው ። ቴናርዲዬም ወጉን ቀጠለ ፤ «ሙሴ ባሮን— በከርሰ ምድሩ ተደብቆ የሚኖረው ሰውዬና ነፍሰ ገዳዩ በመውጫው በር አካባቢ ተገናኙ ። ሰላምታም ተሰጣጡ ። ነፍሰ ገዳዩ በከርሰ ምድር ውስጥ ተሰውሮ የሚኖረውን ሰውዬ እያየ ፤ ‘ምን እንደተሸከምሁ ታያለህ ። ከዚህ ለመውጣት እፈልጋለሁ ። የመውጫው በር ቁልፍ አንተ ዘንድ ስላለ እባክህን ክፈትልኝ’ ሲል ለመነው ። ነፍሰ ገዳዩ ቦጣም ጉልበተኛ ሰው ስለነበረ በከርሰ ምድር የሚኖረው ሰውዬ እምቢ ሊለው አልደፈረም ። ሆኖም መውጫውን በር ከመክፈቱ በፊት አስከሬኑን መረመረው ። የወጣት ልጅ አስከሬን ነበር ። ፊቱም በደም ተበክሎ ነበር ። እንዲሁ አስከሬኑን ሲመረምር ሳለ ነፍሰ ገዳዩ ሳያየው በቅልጥፍና ከአስከሬኑ ብጣሽ ጨርቅ ቀድዶ አወጣለት ። ይኸውም ምናልባት ነፍሰ ገዳዩ ተይዞ ምርመራ ቢካሄድበት ጨርቁ ለማስረጃነት ይጠቅም ይሆናል በሚል ግምት ነው ። ከዚያ በኋላ የመውጫውን በር ለነፍሰ ገዳዩ ከፈተለት ። ነፍሰ ገዳዩ አስከሬኑን ተሸክሞ ከወጣ በኋላ በድብቅ የሚኖረው ሰውዬ መውጫውን በር ከውስጥ ቆልፎት እዚያው ቀረ ፤ በወንጀሉ እንዳይከሰስ ፈርቶ ነው። እኔ ነገሩ አሁን ግልጽ እንደሆነልህ ተስፋ አለኝ ። አስከሬኑን ተሸክሞ የወጣው ነፍሰ ገዳይ ግሪን ቫልፓ ነበር ። በከርሰ ምድር ይኖር የነበረውም ሰውዬ አጠገብህ ተቀምጦ የሚያወጋልህ ቴናርዲዬ ነበር ። ከአስከሬኑ ኩቴ ተቀድዶ የወጣውም ቁራጭ ጨርቅ እነሆ!» ብሎ ጨርቁን ከኪሱ አውጥቶ አሳየው ።

@OLDBOOKSPDF

ማሪዩ ኩሎቀመጠበት ኑጥሮ ተነሳ ። እስከዛሬ ድረስ እንቆቅልሽ ሆኖበት የኖረው ምስጢር ወጣ ብሎ ታየው ። ዓይኑን ከብጣቂው ጨርቅ ሳይነቅል የኋሊት እየተራመደ ሔዶ ቂም ሳጥኑን ከፈተው ።

«ሙሴ ባሮን.....» አለው ቴናርዲዬ ፤ «ጣጋን ቫልገ የገደለው ወጣት የተትረፈረፈው ከበርቴ የነበረ ይመስለኛል ።»

«ተግድኋል ያልከው ወጣት እኔ ነበርኩ!» አለው ማርዩ ፤ «ያን ሁን ለብሼው የነበረውም ኩት ይኸውና!» ብሎ በደም ያደፈውን ኩት ከቂም ሳጥኑ አውጥቶ ወለሉ ላይ ወረወረው ።

ከዚያ በኋላ ቴናርዲዬ ያመጣውን ብጣሽ ጨርቅ ኮቱ ከተቀደደበት ሥፍራ አኑሮ ቢያየው በትክክል የሚገጥም ሆኖ አገኘው ።

ቴናርዲዬ በዚህ ጊዜ ከድንጋጤው የተነሳ እንደሐውልት ደርቆ ቀረ ። ማሪዩም ተጨማሪ ግንዛቤ ወረወረለትና ፥ «ክፉ ሰው ነህ.....» አለው ፤ «የጣጋን ቫልገን ስም ለማጉደፍ ብለህ መጣህ ። ነገር ግን ሳታውቀው ስማቸውን አደስክሳቸው ። ቀጣፊ ሌባ አንተ እንጂ ጣጋ ቫልገ አይደሉም ። አንተ ነህ ነፍሰ ገዳይ! በሎፒታል ጐዳና የፈጸምከውን ወንጀል በዓይኔ አይቻለሁ ። የዓይን ምስክር ሆኛለሁ ። ብፈልግ አስይዤ ወህኒ ቤት እንድትታሠር ፥ ከዚያም የባሰ ነገር እንዲያርስብህ ለማድረግ አችላለሁ ። ነገር ግን አላደርገውም ። አንተ መከረኛ! ለወደፊቱ ቅጣት ይሁንህ ። በል የሰጠሁህን ገንዘብ ይዘህ ከዚህ ውጣልኝ ። የሥተርሉው ውለታህ ባይኖር ኖሮ የማደርገውን ባወቅህ ነበር!»

«ሥተርሉ!» አለ ቴናርዲዬ ፤ ማሪዩ የወረወረለትን ገንዘብ በኪሱ እየጨመረ ።

«አዎን አንተ ነፍሰ ገዳይ! በሥተርሉ የአንድ ኮሎኔል ሕይወት አትርፈሃል ።»

«የጀኔራል ማለትህ ነው?»

«የኮሎኔል ብዬሃለሁ፤ አሁን ከዚህ ውጣልኝ፤ አንካ ደሞ ተጨማሪ ምስት ሺ ፍራንክ..... ሁሉንም ውሰድ ። ነገ ሴት ልጅህን ይዘህ ወዴ አሜሪካን አገር እንድትሄድ ። ሚስትህ እንደሞተች አውቃለሁ ። አንተ ውሽታም፤ ነገ ወደ አሜሪካን አገር ለመሔድ ስትነሳ ሀያ ሺ ፍራንክ በተጨማሪ እስጥሃለሁ ። ከዚህ አገር ግን መውጣት አለብህ!»

ቴናርዲዬ ምስጢር አለኝ ብሎ በተናገረው ሁሉ በአንድ ፊት ሲዋረድ በሌላ ፊት አዲስ የሕይወት ተስፋ አገኘበት ። ሀያ ሺ ፍራንክ ያስፈለገው ወዴ አሜሪካን አገር ሔዶ የባርያ ንግድ ለማካሄድና ወርቅ ለማፈስ ነበር ። ቴናርዲዬ ተስናብቶት ሲወጣ ማሪዩ፤ «ወይ ፈጣሪዬ! ለካስ ሕይወቱን

@OLDBOOKSPDF

ያዳኑልኝ አሳቸው ናቸው!» አሰና ወደ አትክልቱ ቦታ ወጥቶ ፤ «ኮዜት! ኮዜት! »ሲል ተጣራ ፤ «ፊጠን ብለሽ የአንገት ልብስሽን አድርጊ ኮዜት!»

ኮዜት ያለአንዳች ጥያቄ ታዘዘችው ።

ማሪዩ ጐን ቫልጣን በዓይነ ሕሊናው ሲያየው ከምን ጊዜም ይበልጥ ገዝፎ ታየው ። እንደክርስቶስም ቆጠረው ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ማሪዩና ኮዜት ጋሪ ላይ ተሰፍረው መንገድ ጀመሩ ። «ባለጋሪ..... ወደ ሎም አርሜ ጐዳና ንዳ..... ቁጥር ሰባት ቤት.....» አለው ማሪዩ ።

«ውይ! እንዴት ደስ አለኝ!» አለችው ኮዜት ፤ «ወደ ሎም አርሜ ጐዳና ልንሔድ ነው? ሙሴ ጐን ለመጠየቅ.....?»

«አባዬን ለመጠየቅ ብትዪ ይበልጥ አያምርብሽም!» አላት ማሪዩ ፤ «በነገራችን ላይ..... በጋቭሮሽ እጅ የላከሁልሽ ደብዳቤ እንዳልደረሰሽ ነግረሽኝ ነበር ። ደብዳቤው ያልደረሰሽ በአባባ እጅ ቢወድቅ ነው ። አባባ ወደ ምሽጉ የመጡት እኔን ለማዳን መሆን አለበት ። የሌሎችንም ሕይወት አድነዋል ። ሌላ ቀርቶ የጣቬርን ሕይወት አድነውለታል ። እኔን ያዳኑኝ እኔና አንቺ እንድንጋባ ብለው ነው ። እና ምን ዓይነቱ ምስጋና ቢሰ ሰው ነኝ! የአንቺ ጠባቂ ከመሆን አልፈው የእኔም ጠባቂ ሆነዋል ። እስቲ እስ ቢው..... እኔን ተሸክመው ግጥ እንኳ ሳይፈሩ ማጡን አቋርጠው ነው የወጡት! እኔ በዚያን ጊዜ ሕሊናዬን ስቼ ስለነበረ ምንም አላወቅሁም ። ምንም አላየሁም ። ምንምም አልሰማሁም ። ለማንኛውም አሁን ከዚያ እንዲደረ ስን ይዘናቸው መምጣት አለብን ። ቢፈቅዱም ባይፈቅዱም ይዘናቸው መጥ ሪን ከእኛው ጋር ይኖራሉ ። ከአሁን ወዲያ ተለይተውን አይኖሩም ።»

ኮዜት ዝም ብላ ከመሰማት በስተቀር ማሪዩን በድንገት ምን እንደለ ወጠው ለማወቅ አልቻለችም ። እንዲያውም «አብዲል እንዴ?» ስትል አሰበች ፤ ማሪዩ የነገራት ሁሉ ለሷ አዲስ ነገር ነበርና ።

ጋሪው ጉዞውን ቀጠለ ።

— 4 —

የበሩን መንኳኳት ሲሰማ ጐን ቫልጥ ዓይኑን ወደ በሩ መልሶ ፤ «ይግቡ!» አለ። ኮዜት ቀድማ ገባች ። ማሪዩ ቀረት ብሎ ተከትሏት ገባ ።

«ኮዜት!» ብሎ እጁን ዘርግቶ ተቀበላት ጐን ቫልጥ ።

@OLDBOOKSPDF

«አባዬ!» ብላ ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች ከዜት ።

«ከዜት! እውነት አንቺው ነሽ! ይቅርታ አድርገሽልኛላ!»

«አባባ!» አለው ማሪዩ በዚህ ጊዜ ።
«አንተም ይቅርታ አድርገህልኛላ!»

ከዜት ባርኔጣዋን አውልቃ የአንገት ልብሷንም አንሰታ አልጋው ላይ ወረወረቻቸውና የአባቷን ነጭ ጺጉር በእጅዋ ዳበሰ አድርጋ ግምባሩን ሳመችው ።

«ሁለተኛ አላይሽ ይሆናል ብዬ ሰግቼ ነበር ከዜት» አላት ፤ «ወይ የእግዚአብሔር ነገር!»
«በጣም ተለውጠሃል አባዬ! እሞህ ኖሯል?» ብላ ዓይኗን ወደ ማሪዩ መልሳ ፤

«ናና እጄን እየው..... እጄ እንዴት የቀዘቀዘ መስለህ!» አለችው ።

«እና ሙሴ ፖሚርሲ.....ይቅርታ አድርገህልኛላ! ባይሆን ኖሮ ልትጠ ይቅኝ ባልመጣህ ነበር» አለው ዣን ቫልዣ ።

«ከዜት.....አባባ የሚሉትን ትሰሚያለሽ?» አላት ማሪዩ ለከዜት ፣ «ይቅርታ አድርገህልኛላ ይሉኛል ። ታዲያ ሕይወቴን ያዳኑልኝ እሳቸው ናቸው ። ሕይወቴን ከማዳንም አልፈው እንቺን ለኔ ሰጥተውኛል ። ይህንን ሁሉ ካደረጉልኝ በኋላ የበደሉኝ ይመስል ይቅርታ አድርገህልኛላ ይሉኛል ። ከምሽጉ የሄዱት ፡እኔን ጥሽክመው በከርሰ ምድር ውስጥ የተጓዙት፡ ማጥ ውስጥ የገቡት ፡ ሶኤና ላንቺ በማሰብ እንጂ ለራሳቸው ብለው አይደለም ። መልአክ እንጂ ሰው አይደሉም!» አላት ።

«ይህንን ሁሉ ማን አውራ አለህ! ዝም ብትል አይሻልም ኖሯል?» አለው ዣን ቫልዣ ።

«እንድናገርማ ያደረጉኝ እርስዎ ነዎት ። ለመሆኑ ሕይወቴን እንዳዳኑልኝ ለምን ደበቁኝ?»

«እውነቱን ነግሬሃለሁ ።»

«ሙሉውን እውነት አልነገሩኝማ! ከፊሉን ብቻ ነው የነገሩኝ ። ሙሴ ማድሌን እንደነበሩ ለምን አልነገሩኝም! ጐቬርን ነዳ እንደለቀቁት ለምን አልነገሩኝም! ሕይወቴን እንዳዳኑልኝ ለምን አልነገሩኝም!»

«ይህንን ሁሉ ያልነገርኩህ ከእናንተ መገለል ይገባኛል ብዬ በማመኔ ነበር ።»

@OLDBOOKSPDF

«ከአሁን ወዲያ እዚህ የሚቆዩ ይመስሎታል ታዲያ? ይዘንዎት ነው የምንሔደው ። ከአሁን ወዲያ ከእኛ ተግልሰው አይኖሩም ። ነገ እዚህ አሥ ናለሁ ብለው አያስቡ ።»

«ነገ እዚህ አልሆንም ። ከእናንተም ጋር አልሆንም ።»

«እንዴት? አሁንም እንደገና ጉዞ እሔዳለሁ እንዳይሉን!»

«አዎን ። ይዘንህ ነው የምንሄድ አባዬ ። ያዘጋጀንልህ ክፍል አሁንም እየጠበቀህ ነው ።»

«አብረን ብንኖር መልካም በሆነ ነበር ። ብቻ.....» አለ ጎን ቫልጋ ።

«ምንድነው ብቻ!» አለችው ኮዜት ።

«ከአሁን ወዲያ አልኖርም ። ዛሬ እሞታለሁ ።»

ኮዜትና ማሪዩ ደንገጥ አሉ ።
«እሞታለሁ ? ።»
«አዎን ። ብቻ ሞት ምንም አይደለም» አለ ጎን ቫልጋ ።

«አባዬ..... እትሞትም! ትኖራለህ!» አለችው ኮዜት ።
«ከመምጣታችሁ በፊት በሞት ጉዳና ላይ ነበርኩ ። እናንተ ከጣባችሁ በኋላ ግን ቫል አለኝ ። የተሐድሶ ስሜት ተሰማኝ ። »

«ሕያው ነዎት » አሰው ማሪዩ ፤ «አንዴርስዎ ያለ ሕያው ሰው በቀላሉ አይሞትም ። ይኖራሉ ። ከእኛ ጋር ሆነው ረጅም ጊዜ ይኖራሉ ።»

ጎን ቫልጋ ፈገግ ብሎ ይናገር ጀመር ፤ «ብሞት ይሻለኛል ። እግዚ አብሔር ጠርቶኛል ። የሚሻለኝን የሚያውቅ ደሞ እሱ ነው ። ለናንተ ግን የደስታ ኑሮ እመኛላችኋለሁ ።»

በዚህ ጊዜ ድምጽ ሰሙ ። ሐኪሙ ተመልሶ መምጣቱ ነበር ። ሐኪሙ ሲገባ ፤ «እንደምን ዋሉ ዶክተር.....? እኔህ የሚያይዋቸው ልጆቼ ናቸው» አለው ጎን ቫልጋ ።

ዶክተሩ የጎን ቫልጋን የደም ምት እጁን ያዝ አድርጎ መረመረው ። ዓይኑንም ወደእነ ኮዜት መልሶ ፤ «እናንተን ኖሯል ለማየት የፈለጉት!» አለ ። ጐንበስ ብሎም በማሪዩ ጆሮ ፤ «አልቆላቸዋል»! አለው ።

ጎን ቫልጋ በድንገት ተነሰቶ ቆመ ። ማሪዩና ዶክተሩ እንዳይወድቅ ሊይዙት ሞከሩ ። እሱ ግን እጆቸውን ገፉ አደረገና ወደ ግድግዳው ሔድ

@OLDBOOKSPDF

አለ ። በግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የመዳብ መስቀል አውርዶ ተመልሶ ወደ ወንበሩ መጣ ። «ታላቁ ሰማዕት ይህ ነው!» አለ መስቀሉን እያየ ።

ከዚያ በኋላ እየተዳከመ ሄደ ጣን ቫልጣ ። «አባዬ..... አውነት ልናጣህ ነው!» አለችው ከዚት እምባዋን እያፈሰሰች ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን እንደ ገና ነፍስ ዘራ ። የከዚትን ቀሚስ እጅጌውን ያዝ አድርጎ ሳመው ።

«እየተሻላቸው ናቸው.....እየተሻላቸው ናቸው ዶክተር» አለ ማሪዬ ።

«ያሳዘኑኝ ነገር ምን እንደሆነ ለሁሉታችሁም ልነግራችሁ እወዳለሁ ሙሴ ፖሚርሲ.....» አለ ጣን ቫልጣ ፤ «ያሳዘኑኝ ነገር ገንዘቡን አለመንካ ታችሁ ነው ። ገንዘቡ የከዚት አንጡራ ሀብቷ ነው ። የጥቁር መስተዋት ጌጥ በርካሽ ሊሠራ የሚያስችል ዘዴ በመፍጠሬ ላፈራው የቻልሀት ሀብት ነው ። ዝርዝሩን በዚህ ወረቀት ጽፌ አስቀርቼላችኋለሁ ። ሀብቱ እንዴት እንደተገኘ የምገልጽላችሁ ሕሊናችሁ ሳይቆረቁራችሁ እንድትገለገሉበት ነው ።»

በዚህ ጊዜ የበረኛው ሚስት ወደ ፎቁ መጥታ በከፊል በተከፈተው በር ስታይ ነበረች ። ዶክተሩ እንድትሔድ ነገራት ። ከመሔዷ በፊት ግን ፤ «ቄስ እንዲጠራልዎ ይወዳሉ?» ስትል ጣን ቫልጣን ጠየቀችው ።

«ከቄስ ጋር ተግናኝቻለሁ..... አያስፈልግም» አላት ። ይህን በሚልበት ጊዜ አቡነ ሚሪዬል በዓይነ ሕሊናው ሳይታዬት አልቀሩም ።

«እና ቅር የሚያሰኙትሁ እንዳችም ነገር የለም» ሲል ቀጠለ ጣን ቫልጣ ፤ «ሀብቱ በትክክለኛ መንገድ እንጂ በተጭበረበረ ሁኔታ የተገኘ ስላልሆነ ሕሊናችሁን አዝናንታችሁ ተደሰቱበት» አሳቸው ።

ጣን ቫልጣ ይበልጥ እየተዳከመ ሔደ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይል ገባ ። ክንዱን ማንቀሳቀስ ተሳነው ። እግሮቹንም እንዲሁ ። ሕይወት እየከዳው ሔደ ።

ከዚትና ማሪዬ ጠጋ እንዲሉለት ምልክት ሰጣቸው ። የመጨረሻው ሰዓት ተቃርቦ ነበር ። «በጣም ነው የማፈቅራችሁ» አላቸው በሞተ ድምጽ ፤ «በዚህ ሁኔታ ሆኖ መሞት እንዴት ደስ ይላል! ከሞትሁ በኋላ ትንሽ ታለቅሺልኛለሽ ከዚት ። ብዙ ግን እንዳይሆን ። እና ሁለታችሁም ተደሰታችሁ ኑሩ ልጆቼ ። በወረሳችሁት ገንዘብ ተደሰቱበት ። የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ግዙበት ። ንጹህ ገንዘብ ነው..... በንጹህ ሥራ የተገኘ ። በጢስ ማውጫው መደርደሪያ ላይ ያሉትንም የሻማ መቅረዞች ውሰዷቸው ። ከብር የተሠሩ ናቸው ። እኔ ግን ከወርቅ ወይም ከእንቁ እንደተሠሩ አቆጥራቸዋለሁ ። እነዚህን መቅረዞች የሰጡኝ አቡን በሰማይ ቤት ሆነው ተደስተውብኝ እንደሆነ አላውቅም ። እኔ ግን የተቻለኝን ሁሉ አድርጌአለሁ ። ልጆቼ በድህነት እንደኖርኩ ታውቃላችሁ ። ድሆች ከሚቀበሩበትም ሥፍራ እንድትቀብሩኝ ፈቃዴ ነው ። መቃብሬ ላይ ባለ ድንጋይ ስሜ እንዲጻፍበት

@OLDBOOKSPDF

አልፈልግም ። ከዚት..... አልፎ አልፎ መጥተሽ መቃብሬን ብትነበኚው ደስ ይለኛል ። አንተም እንዲሁ ሙሴ ፖሚርሲ ። ቀደም ብዬ አልወድህም ነበር ። ይህንን መናዘዝ ይገባኛል ። ይቅርታ እንድታደርግሻለም አለምን ሀለሁ ። አሁን ግን የከዚትን ያህል እወድሃለሁ ። ከዚትን እንደምታስደስ ታት ተስፋ አለኝ ። ጠረፌዘው መሳቢያ ውስጥ አምስት መቶ ፍራንክ አለኝ ። ሲድሆች የሚሰጥ ነው። ብሎ ፤ ከከዚት አልጋው ላይ ያለውን ልብስ አይተሸዋል? የድሮ ልብስሽ ነው ። ጊዜው እንዴት ይሮጣል! እኔና አንቺ የተገናኘነው ከአስር ዓመት በላይ ሆኗል ። ምንሪርመይን ታስታውሺዋለሽ ከዚት? ሚካ ውስጥ ውሃ ለመቅዳት የወረድሽበትን ቀን ታስታውሽዋለሽ? ያን ቀን ሲሲት ምን ያህል ፈርተሽ ነበር! ባልዴሽን ከእጅሽ ወስጄ በእጄ እንዳንጠለጠልኩት ትዝ ይልሻል? አሸንጉሊቷስ ትዝ ትልሻለች? ካትሪን ብለሽ ነበር የምትጠሪያት ። ያ ሁሉ ያለፈ ነገር ነው ። እኩናርዴይ በጎ ስዎች አልነበሩም ። ዬሁን እንጂ ይቅር በያቸው ። እና የወላጅ እናትሽን ስም እስካሁን ድረስ አልነገርኩሽም ። የምነግርሽ ጊዜው አሁን ነው ። ፋንቲን ትባል ነበር ። ተሰቃይታ ነው የሞረችው ። አንቺን ግን እጅግ በጣም ታፈቅርሽ ነበር ። አንቺ ተደስተሽ አንድትኖሪ እግዚአብሔር ፈቅዶል ሻል ። እናትሽ ግን ተደስታ እንዳትኖር ሳይፈቅድላት ቀረ ። የእግዚአብ ሔርን ሥራ ማን ያውቃል! እሱ የሚሠራውን የሚያውቅ እሱ ራሱ ብቻ ነው ። በተረፈ ጊዜዬ ደርሷለሽ ። ሁሌም ቢሆን ተፋቀሩ ልጆቼ ። ከፍቅር የበለጠ ነገር የለም ። እና አሁን ዓይኔ እየጨለመ ሄዷል ። ይበልጥ ጠጋ በሉልኝ ። ደስ ብሎኛ ነው የምሞተው ። ጠጋ በሉልኝና እጂን ስመጨረሻ ጊዜ ራሳቸሁ ላይ ላሳርፍባቸው ።»

ከዚትና ማርዩ እነሳ እየተናነቃቸው ራሳቸውን ሰጠው ። አንድ እጁን በከዚት ራስ ላይ ሌላ እጁን በማሪዩ ራስ ላይ አሳረፋቸው ። ከዚያ በኋላ እጆቹ አልተንቀሳቀሱም ። ሕይወቱ አለፈች ።

በጉር ቁሸዝ መካነ መቃብር ፣ ተራ ሰዎች በሚቀበሩበት ክፍል ተቀ በረ ጣን ሻልማ ። በመቃብሩ ላይ ደግጋይ ተጫነበት ። ጊዜው ውሎ ሲያ ድር ድንጋዩ እርጥበት እያጠቃው ሔደ ። አረንጓዴ ጥክል የሚመስል ነገር ወደተቧት ። ወርች ፡ተሳቸውን ጣለባት ። ሣር ቅጠልም በቀለበት.....

@OLDBOOKSPDF